ገዛዔ



ልዩ ዕትም

ቀራንዮ!

ሞት የሞተበት!

አዳም ሲበድል ሞት ወደ ምድር ገባ። የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ዕጽዋት፣ እንስሳት፣ የባህር ፍጡራን፣ የሰማይ ወፎች፣ ወዘተ በሙሉ ሟች ሆኑ። ምድር እሾህ እንድታበቅል ተረገመች፤ አየሩ በሞት ታወደ፤ የሞት ማዳበሪያ አፈሩን አረከሰው፤ የሞት መውጊያ እያንዳንዱን ፍጡር ነደፈ፤ ፍጡርም ከሞት ማምለጥ የማይችል ዓቅመቢስ ሆነ፤ የፍጥረት የመጨረሻ ማስፈራሪያ ሞት ሆነ፤ ሞት በሕይወት ላይ አጓራ፤ ፍጥረትም በፍርሃት አንገቱን ደፋ፤ ሞት በማናለብኝነት በሕይወት ላይ ነገሠ።

አዳም የግዛት ሥልጣኑን አስረክቦ ሞት በነገሠበት ጊዜ እግዚአብሔር ሞትን ድል እንደሚያደረግ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው የሴቲቱ ዘር በሆነው በጌታችንና መድኃኒታችን ክርስቶስ እንደሆነ ሲናገር እንዲህ አለ፤ “እርሱ (ጌታችን) ራስህን (የሰይጣንን) ይቀጠቅጣል፥ አንተም (እባቡ ወይም ሰይጣን) ሰኰናውን (ተረከዙን) ትቀጠቅጣለህ” (ዘፍጥረት 3፡15)። ሞት በሕይወት ላይ ደረቱን ነፍቶ የበላይነቱን ለዘላለም ሳይጎናጸፍ ገና ከጅምሩ ኪሣራ ገጠመው፤ ሕልሙ ቅዠት ሆነ። የሴቲቱ ዘር የሆነው መድኅን ክርስቶስ በሞቱ ሞትን ይቀጠቅጠዋል፣ ይገድለዋል በማለት ኃያሉ አምላክ እግዚአብሔር በሥልጣን ተናገረ።

ይህንን ተስፋ የአዳም ቀጣይ ዘሮች ለመቀበል አዳገታቸው፤ ኃጢአትን መረጡ፤ ሞትን አነገሡ። የእግዚአብሔር ተቃዋሚ ሆኑ፤ ከፋታቸው በዛ፤ የልባቸው አሳብና ምኞት ያለማቋረጥ ሁልጊዜ ክፉ ሆነ (ዘፍጥረት 6፡5)።

ዲያቢሎስና የሥጋቸው ሃሳብ ሽምጥ ሲጋልባቸው የነበሩ እነዚህ ሰዎች፤ በክፉ ተግባራቸው የመሲሑን መምጫ መንገድ አጥብበው በሰፊው ጎዳና ወደ ሞት ነጎዱ። እግዚአብሔር ግን ያቺን የጠበበች መንገድ ጠብቆ የመሢህ መምጫ አደረጋት። “የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ (ገላትያ 4፡4)።

የሴቲቱ ዘር የሆነው መሢሕ ጌታ ወደዚህች ምድር መጥቶ፣ ነቁጥ አልባ ፍጹምና ንጹህ ሕይወት ኖሮ፣ በጠላት ወረዳ ውስጥ ብቻውን ሞትን ተጋፈጠ፤ የምድርን የእሾህ ዕርግማን አክሊሉ አድርጎ ከፍ ብሎ ታየ፤ ፍጥረተ ዓለም ሁሉ በገሃድ እያየው ዲያቢሎስንና ሞትን በቀራንዮ ከፍታ ላይ ግብግብ ገጠመ፤ **ሞትን ለዘላለም ለመግደል ሕይወቱን ለዘላለም አሳልፎ ሰጠ**፤ “ተፈጸመ” በማለት ሞትን በሞቱ ድል ነሳ። ለኃጢአት የሚገባውን መስዋዕትነት በመክፈል የእባቡን ጭንቅላት ቀጠቀጠ። በቀራንዮ ኮረብታ ሞት ሞተ።

ጌታችንን ከመስቀል አውርደው በመቃብር ባኖሩት ጊዜ ተስፋ ያልቆረጠው ሞት ከሲዖል (መቃብር) ጋር ሆነው ጌታችንን በመቃብሩ አሸገው ለማኖር አሤሩ። እርሱ ግን ሰንበትን እንደ ትዕዛዙ በመቃብር ካሳለፈ በኋላ እሁድ ጠዋት “ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?” በማለት ሞትን በትንሣኤ ጦር ወጋው፤ መቃብርንም ወደራሱ መቃብር በመከተት የአዳምን ዘር ከሞት ኩነኔ ነጻ አወጣው።

ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ወደዚህች ምድር ህጻን ሆኖ በመወለድ ሞትን ብቻውን በመጋፈጥ ድል ያደረገው መድኅናችን፤ በሞት ላይ የመጨረሻውን ምት ለመሠንዘር የክብር አክሊል ተጎናጽፎ፣ የነገሥታት ንጉሥ ሆኖ ይመጣል። ከዚያም የመጨረሻው መጨረሻ ሲሆን፣ በጻድቃንና ኃጥዓን ላይ የመጨረሻው ውሳኔ ሲሰጥ የፍጻሜው ፍጻሜ ይሆናል። ሞትና መቃብርም በእሣት ባሕር ይጣላሉ (ራዕይ 20፡14)፤ የሕይወት መዓዛ አየሩን ይሞላዋል፤ ሰብዓዊ ፍጡርና ተፈጥሮ በአንድ ላይ ሞትን ድል ላደረገው አምላካቸው ይቀኛሉ፤ “እግዚአብሔር ፍቅር ነው” በማለት ለዘላለም ያዜማሉ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

አዘጋጆቹ

ማዉጫ

ለቅሶ በሆሣዕና! 4

ቀራንዮ - ሞት የሞተበት! 7

“ጌታ ተነስቷል!” 18

ሞኝነት ወይስ ...? 22

ቀራንዮና ኮሮና 24

ጥያቄና መልስ 26

የሽፋን ፎቶ፤ Pamela Maxwell 123RF

“ስለዚህ ጊዜው መቼ እንደሚሆን ኢታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፣ ጸልዩም” ማርቆስ 13፡33

ጊዜው መጽሔት የመጨረሻው ዘመን መድረሱን ለማስገንዘብና ለማስጠንቀቅ መልዕክት የምታቀርብ እንደመሆኗ የመጽሔቷ ስም ዓርማው ውስጥ ተካትቷል፡፡ ከሥሩ የሚታየው ጥሩምባ ከመልዕክቱ በፊት ንቃት እንዲኖር የሚሰማ የማንቂያ ድምጽ ማመላከቻ ነው፡፡

አዘጋጆች፤
ዳዊት መሐሪ
ድርባ ፈቃዱ
ዘውዱ ሰብለወርቅ
ጥበበሥላሴ መንግሥቱ
አምደኞች፤
ፓ/ር አገኘሁ ወንድም
ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ
ሽያጭና ስርጭት
ልዝቤ ፈንታሁን
ወገን ፈጠነ
ምንትዋብ ሰብለወርቅ
Logo Design and Layout: Danny Monnie

አድራሻ፤
ኢሜይል፤ editor@giziew.org
ስልክ: 911-918194/911-335790/911-373097
መ.ሳ.ቁ. 438፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Facebook: fb.me/giziew7
ከአገር ውጪ ለመደወልና ለመጻፍ: +1 314 499-8477
Viber: +1 785 730-4800
Whatsapp and Telegram: +1 314 499-8477
Website: http://www.giziew.org/

በተለይ እስካልተጠቀሰ በዚህ መጽሔት ውስጥ የተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት አኤአ በ1962 ከታተመውና ከአዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ነው።

የጊዜው መጽሔት ዓላማ:
መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት፤ መድኃኒዓለምን ማዕከል ያደረገ የወንጌል መልዕክት ማቅረብ።

ከቅሶ በሆሣዕና!

ጥበበሥላሴ መንግሥቱ

ትንቢቱ የተነገረው ከ500 ዓመት በፊት ነበር፤ እንዲህ የሚለው “አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፥ እልል በዪ፤ እነሆ፥ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያይቱ ግልገል በውርጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል” (ዘካርያስ 9፡9)። ሆኖም ይህ “ደስ ይበልሽ” ተብሎ የተተነበየ የደስታ፣ የሆሳዕና መዝሙር በልቅሶ ተቀየረ!

ጌታችንና መድኃኒታችን የማርታና የማርያምን ወንድም አልዓዛርን ከሞት ባስነሳባት ጊዜ የሁሉም ትኩረት ከበፊቱ በበለጠ በእርሱ ላይ ሆነ። የካህናት አለቆችና ጸረ-መድኃኒዓለም የነበሩት ሁሉ በሽብር ተሞሉ፤ አልዓዛር ከሞተ ከአራት ቀን በኋላ እንዴት ሊነሳ ቻለ? ምን ዓይነት ኃይል ቢኖረው ነው ይህንን ማድረግ የቻለው? ይህንን መደበቅና ማስተባበል አንችልም፤ እርምጃ መውሰድ አለብን፤ አልዓዛርን መግደል አለብን፤ አልዓዛርንም ብቻ ሳይሆን ራሱን ከርስቶስን ማስወገድ አለብን በማለት ተማከሩ (ዮሐ. 11፡53፤ 12፡10)።

ጌታችን ከርስቶስ አልዓዛርን ከሞት ካስነሳ በኋላ ከቢታኒያ ወደ ኤፍሬም ከተማ ሔደ፤ ከዚያም ፋሲካ ከመሆኑ ከስድስት ቀን በፊት ወደ ቢታኒያ ተመልሶ መጣ። በዚያም የእራት ግብዣ በተደረገለት ጊዜ ማርያም “እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጒርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ” (ዮሐንስ 12፡3)። በሁኔታው ያልተደሰተው ይሁዳ ሽቶው ተሸጦ ለድሆች መርጃ መዋል ነበረበት የሚል ተቃውሞ አቀረበ። ጌታችን ሲመልስም “ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ” (ዮሐ. 12፡8)።

በማግስቱ ግን የመሲሕን በዳዊት ዙፋን መቀመጥ የሚያበስር ከ500 ዓመታት በፊት የተተነበየ ትንቢት የሚፈጸምበት አንድ ታላቅ ትዕይንተ ሕዝብ ተካሄደ። እጅግ በርካታ ሕዝብ በአልዓዛር መነሳት ወሬውን ሰምቶ እየተደነቀ የነበረ ሲሆን ከዚያም ሌላ የፋሲካ በዓል ሊከበር ጥቂት ቀናት ስለቀሩት የሕዝቡ ቁጥር ከመጠን በላይ ነበር። ብዙ ጊዜ ራሱን በመደበቅ አገልግሎቱን ይፈጽም የነበረው ጌታችንና መድኃኒታችን አሁን ግን አንድ ያልተጠበቀ ትዕይንት እንዲሆን ፈቀደ።



“በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ ወደ እርስዋም ገብታችሁ ከሰው ማንም ገና ያልተቀመጠበት ውርንጫ ታስሮ ታገኛላችሁ፥ ፈትታችሁም አምጡት” በማለት ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ ትዕዛዝ ሰጠ (ሉቃስ 19፡30)። ውርንጫዋ መጥታ እንደተቀመጠባት የአካባቢው ድባብ ተቀየረ። ብርና ወርቅ ሁሉ የእርሱ የሆነው የፍጥረተዓለም ገዢ፣ ወደዚህ ምድር ሲመጣ በከብቶች ግርግም ተወለደ፤ “የምድረ በዳ አራዊት ሁሉ በሺህ ተራራዎች ያሉ እንስሶችም የእኔ ናቸውና” ያለው የነገሥታት ንጉሥ፣ በዳዊት ዙፋን ንግሥናን ሲቀበል በተውሶ በተገኘች አንዲት ውርንጫ ላይ ተቀመጠ (መዝ. 50፡10)።

እስከዚህ ቀን ድረስ በእግሩ በየቦታው ሲጓዝ የነበረው ጌታ አሁን ግን ሌላ መጓጓዣ ተጠቀመ፤ ውርንጫዋን በመምራት ፊት አውራሪው ደግሞ አልዓዛር ነበር። በሁኔታው ደቀመዛሙርት ተደንቀዋል። ነገርግን ሰዎች በመሰባሰብ ደስታቸውን መግለጽ ሲጀምሩ ትዕይንቱ እየተቀየረ መጣ። ወዲያውም የሕዝቡ ቁጥር እየጨመረ ብቻ ሳይሆን ሁኔታውም ሌላ መልክ ያዘ። እጅግ በርካታ ሰዎች ልብሳቸውን፣ የዛፍ ቅጠሎችን እና የዘንባባ ዝንጣፊን መንገዱ ላይ እያነጠፉ በዝማሬና በዕልልታ እንዲህ እያሉ ተከተሉት፤ **“ሆሣዕና ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወንጉሥሙ ለእስራኤል”።**

የሙቶ ዓመታት ትንቢትን በዓይናቸው ሲፈጸም ስላዩ ነበር “ሆሣዕና፤ በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው” በማለት የጮኹት። ተስፋ የተደረገበት መሢሕ፣ በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጠው ጌታ፣ ከሮም ቀንበር እስራኤልን ነጻ የሚያወጣው ታዳጊ፣ ኢየሩሳሌምን መቀመጫው አድርጎ በዳዊት ዙፋን ላይ የሚነግሠው

የተባረከው የእስራኤል ንጉሥ። “በጌታ ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት፤ ሆሣዕና በአርያም” በማለት አስጮኻቸው (ማር. ፲፡፲)።

ከዚህ ስብስብ ውስጥ አልዓዛርን ከሙታን ሲያስነሳው ዓይተው የመሰከሩ ነበሩ፤ ዝናውንም በየአገሩ የበተኑ፣ ያንንም ሰምተው ስብስቡን የተቀላቀሉ በዚህ ትዕይንተ ሕዝብ ውስጥ ነበሩ። ከኢጋንንት ኃይል ነጻ ያወጣቸው በትዕይንቱ ውስጥ ነበሩ፤ ከእነርሱም ሌላ የዓይን ብርሃናቸው የተመለሰላቸው፤ ጆሯቸው የተከፈተላቸው፤ የታሠረው ምላሳቸው የተፈታላቸው፤ ለዓመታት ሽባ ሆነው አሁን ግን እንደልባቸው መንቀሳቀስ የተቻላቸው፤ በማኅበራዊ ፈቀቅታ እና በኳራንቲን ተጽዕኖ “እርኩስ ነኝ” እያሉ ከሁሉ ተለይተው የዳዊት ልጅ አንጽቷቸው ወደ ሕዝብ የተቀላቀሉ፤ መጽናናትን የተቀበሉ መበለቶችና ወላጅ አልባዎች፤ ኃጢአታቸው የተሰረየላቸው፤ ከመናቅ ወደ ክብር፤ ከሐዘን ወደ ሐሴት፤ ከውርደት ወደ ከፍታ፤ ከሞት ወደ ሕይወት የመጡና ሌሎችም እጅግ በርካታ ሰዎች ነበሩ።

እነዚህ ማንም መካድ በማይችልበት መንገድ የጌታችንን አዳኝነትና ኃያልነት የሚመሰክሩ ሆነው በቦታው መገኘታቸው ብዙዎችን እንዲያምኑ ሲያደርጋቸው፤ በፍርሃት ያራዳቸውና ሌላ ሚራ እንዲወጥኑ ያደረጋቸውም ነበሩ። አንዳንድ የጨነቃቸው ፈሪሣውያን ግን “መምህር ሆይ፥ ደቀ መዘሙርትህን ገሥጻቸው” ሲሉት ጌታም “እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ አላቸው” (ሉቃስ ፲፱፡ 39፤40)። ይህንን ትዕይንትና የሕዝብ ማዕበል በዘመኑ በነበረ ዓድማ በታኝም ሆነ ሌላ ኃይል መቋቋም እንደማይችሉ የተረዱ ግን ዕልልታውን ወደ ሐዘን ለመቀየር ቆርጠው ተነሱ።

ጉዞው በየመንገዱ በርካታዎችን እየጨመረ ወደ ኢየሩሳሌም ሲቀጥል የካህናት አለቆችና ፈሪሣውያን በፍጥነት




ወደ ውሳኔ የሚያደርሳቸውን ሚራ ማዋቀር ጀመሩ። “አንድ ስንኳ ልታደርጉ እንዳይቻላችሁ ታያላችሁን? እነሆ፥ ዓለሙ በኋላው ተከትሎት ሄዶአል ተባባሉ” (ዮሐ. ፲፪፡፲፱)። በወቅቱ በነበራቸው ማኅበራዊ መስተጋብር ጉዳዩ በፍጥነት የአይሁድ ሸንጎ አባላት ዘንድ እንዲደርስ ተደረገ። አልዓዛርን ከሞት በማስነሳቱ አልዓዛርንም ጌታችንንም ለመግደል የተወጠነው ሚራ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት መመሪያ ተላለፈ።

የትዕይንቱ ማብቂያ ወደሆነው የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ሲደርስ ሁኔታዎች መቀየር ጀመሩ። በዕልልታና በዝማሬ የተከተለው ሕዝብ ፈጽሞ ያልጠበቀውን ነገር ከጌታችን ፊት ላይ ተመለከተ። ኢየሩሳሌም ንጉሧን ለመቀበል ዝግጅት ብቻ ሳይሆን ፍላጎትም አልነበራትም። ወደ ኢየሩሣሌም “ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት” (ሉቃስ ፲፱፡41)። ያለቀሰው በፊቱ ቀራንዮ ስለታየው፤ ወይም የሚደርስበት ስቃይና መከራ አስጨንቆት አልነበረም።

ያለቀሰው “እንዲህ እያለ” ነበር፦ “ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ፤ አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል። ወራት ይመጣብሻልና፥ ጠላቶችሽም ቅጥር ይቀጥሩብሻል ይከቡሻልም በየበኵሉም ያስጨንቁሻል፤ አንቺንም በአንቺም ውስጥ የሚኖሩትን ልጆችሽን ወደ ታች ይጥላሉ፥ በአንቺ ውስጥም ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተዉም፥ የመጐበኘትሽን ዘመን አላወቅሽምና” (ሉቃስ ፲፱፡42 – 44)።

የመነበኛቷ ዘመን እንዲመጣ እጅግ ብዙዎች ተመኝተዋል፤ ቃትተዋል፤ አልቅሰዋል። ኢየሩሳሌም ግን በአምላኳ ላይ ማመጿን አላቆመችም፤ እንዲያውም ለበርካታ ዓመታት ይህንን አቃልላ ስትመለከት ኖራለች። ኃጢአቷ ከፍቶ “ፈረሶቻቸውም ከነብር ይልቅ ፈጣን፤ ከማታም ተኵላ ይልቅ ጨካኝ፤ ለመብልም እንደሚቸኵል ንስር” የሆኑት ባቢሎናውያን ከሩቅ መጥተው ከተማዋንና ቤተመቅደሱን ከማፍረሳቸው በፊት ነቢያት እያለቀሱ የተናገሩላትን ትንቢት ናቀች (ዕንባቆም ፲፡8)። ይልቁንም ነቢያቶቿን ገደለች፤ አሳደደች። በባቢሎን ከፈረሰች በኋላ እንደገና እንድትሠራ እጅግ በርካታዎች ለፍተዋል፤ እነዘሩባቤልና ዕዝራ መከራ አይተዋል፤ እነ ነህምያ አልቅሰዋል።

አሁን ደግሞ ለምህረት የተዘረጋውን እጁን አልቀበልም ስላለችው ከተማ ጌታችን አለቀሰ፤ ዓመጸኝነቷ የሚያመጣባትን ውድመት አይቶ አለቀሰ፤ ዕብሪተኛነቷ የሚያስከትልባትን ጥፋት አሻግሮ ተመልክቶ አለቀሰ፤ የእግዚአብሔርን ልጅ፤ የዓለምን መድኃኒት አልቀበልም በማለቷ አለቀሰ፤ ከዚህ ሌላ አንዳችም መዳኛ እንደሌላት ዓይቶ አለቀሰ፤ ሆኅዕና በለቅሶ ተቀየረ!



ዓመጸኛዋ ኢየሩሳሌም ጌታዋን ሰቀለች፤ ቀጥላም ጻድቁን እስጢፋኖስን ወገረች፤ ሃዋሪያትን አሳደደች፤ በግፍ ላይ ግፍን አከማቸች፤ ፈውስ እስከማይገኝላት ድረስ ፈጣሪዋን ካደች፤ ምህረትን ናቀች። ዓመታትን ጠብቆ የተናቀው ምህረት ፍትሕን ወለደ። ኢየሩሣሌም በአረመኔው ሮም ወደሙች፤ መቅደሱም ዓመድ ሆነ።

በሰሙነ ሕማማት፣ በስቅለትና በፋሲካ የጌታችንና የመድኃኒታችንን መሐሪነት ስናስብ ሆሳዕና ልንል እንችላለን፤ ተገቢም ነው። ነገርግን ሆሳዕናው ወደ ልቅሶ የሚቀየርበት ጊዜ ደርሶ ይሆን? ትኩረት ሰጥተን እናስብ። የእግዚአብሔር ምህረት ሁልጊዜ ያለገደብ የሚቀጥል አድርገን በመገመት አቅልለን እንዳናየው የሆሳዕና ትዕይንት ያስተምረናል። ምህረት የሚያበቃበት ጊዜ ይመጣል። ፍትሕ ቦታውን የሚወስድበት ቀን አለ። ጻድቅ ፈራጅ የሆነው አምላካችን ለዓለማችን፣ ለአገራችን፣ ለከተማችን፣ ለሕዝባችን፣ ለራሳችን እንደ ኢየሩሳሌም ሳያለቅስልን ምህረቱን አሁን እንቀበልና በመንገዱ እንሂድ።

“እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ” (ዮሐ. 12፡32)። ጌታችንና መድኃኒታችን አሁንም ወደ እርሱ ሊስበን ይፈልጋል፤ ይጥራል። በፍቅር ውስጥ ማስገደድ ስለሌለ ፈጽሞ አያስገድድም። ሆሳዕና ወደ ለቅሶ ሳይቀየር የምህረት ጥሪውን እንስማ፤ ንሰሃ እንግባ፤ ለእርሱም እንታዘዝ። ገዜው

ጥያቄና መልስ

1. በዚህ ምድር ላይ የመጀመሪያው የሰይጣን ውሸት ምንድን ነበር?

“እባብም ለሴቲቱ አላት፦ **ሞትን አትሞቱም**” (ዘፍ. 3፡4)። “ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፤ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ” (ራዕይ 12፡9)። በኤድን ገነት ሔዋንን ያሳታት “እባብ” ተብሎ የተጠቀሰው ሰይጣን ዲያብሎስ እንደሆነ ራዕይ 12፡9 ተርጉሞታል። በወቅቱም ሰይጣን በእባብ ተመስሎ ለሔዋን ያላትና የመጀመሪያው ውሸት “አትሞቱም” የሚለው ነበር፤ እግዚአብሔር ግን “ከፍሬዋ በበላችሁ ጊዜ ሞትን ትሞታላች” ብሎ ነበር። አሁንም ከዋንኞቹ የሰይጣንን ማሳሳቻ ትምህርቶች አንዱ “አትሞቱም” የሚለው ሲሆን ይህም ማለት ሰው ሲሞት ነፍሱ ወደ ገነት ወይም ወደ ሲዖል ትሄዳለች፣ ነፍስ አትሞትም፣ ከሙታን ጋር እናነጋለን፣ ወዘተ የሚባሉት የክርስትናን ካባ የደረቡ ትምህርቶች ናቸው። (ለምሳሌ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማንበብ ይጠቅመናል፤ የግብፅ አስማተኞችና ጠንቋዮች—ዘፀ. 7፡11፤ በዓይንዶር የምትገኘዋ መናፍስት ጠሪ—1ሳሙ. 28፡3-25፤ የባቢሎን ጠንቋዮች—ዳን. 2፡2፤ የምዋርተኝነት መንፈስ የነበረባት አንዲት ሴት—ሐዋ.16፡16-18)።



ሰይጣን - እንደ ብርሃን መልአክ፤ ሰይጣንና መላዕክቱ እጅግ በርካታ ሰዎችን ለማታለል በፊት የሞቱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያትን፣ ሐዋርያትንና ቅዱሳንን በመምሰል የብርሃን መልአክ መስሎ ይገለጻል፤ “...ሰይጣን ራሱ **የብርሃን መልአክ** ለመምሰል ራሱን ይለዋውጣል” (2ቆሮ.11፡13)። እንዲሁ በተዓምራት ሰዎችን ለመጥለፍ በረቀቀ መልኩ ሰይጣን ይጠቀማል። የተለያዩ በሽታዎችን “ፈውስ” አስመልክቶ “ተዓምራት” ከማድረግ ጀምሮ ሙታንን ያስነሳ እስኪመስል ድንቆችን ያደርጋል። በመሆኑም “ሙታን በሆነ መልኩ በሕይወት አሉ፤ ነፍሳቸው አልሞተችም” ብለው የሚያምኑ ሰዎች በእንደዚህ ዓይነቱ የሰይጣን ማታለያ ተጠልፎ ለመውደቅ በጣም ቅርብ ናቸው። (ሙታን ግን የት ናቸው? ነፍስ ምንድነው? ... ገጽ 23ና 26 ላይ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማንሳት እንመልሳለን)

ቀራንዮ - ሞት የሞተበት!

“ቀራንዮ ወይም የራስ ቅል ወደ ተባለ ስፍራም በደረሱ ጊዜ በዚያ ኢየሱስን ሰቀሉት”። “እንዲሁም ኢየሱስ ህዝቡን በገዛ ራሱ ደም ለመቀደስ ከከተማው በር ውጭ መከራን ተቀበለ” (ዕብ. 13፡12)። የእግዚአብሔርን ህግ በመተላለፋቸው አዳምና ሄዋን ከኤደን ተባረሩ። የእኛ ቤዛ የሆነው የሱስ ከኢየሩሳሌም ከልል ውጭ መሰቃየት ነበረበት። ከባድ ወንጀለኞችና ነፍሰ ገዳዮች በሚገደሉበት ከከተማው በር ውጭ ሞተ። “ክርስቶስ ስለእኛ እንደ እርግማን ሆኖ ከህግ እርግማን ዋጀን፥” የሚለው አነጋገር ትልቅ ትርጉም ያለው ነው (ገላ.3፡13)።

የሱስ ከፍርድ አዳራሹ ወጥቶ ወደ ቀራንዮ በተወሰደ ጊዜ እጅግ ብዙ ሕዝብ ተከተለው። የሞት ፍርድ እንደተፈረደበት ወሬው በመላው ኢየሩሳሌም ስለተሰማ ከጎበረተሰቡ በተለያየ ደረጃ የሚኖረው ሕዝብ ወደ መሰቀያው ቦታ ጎረፈ። ካህናቱና ሹማምንቱ ክርስቶስ በእጃቸው እንዲገባ ከተደረገ በክርስቶስ ተከታዮች ላይ ጉዳት ላለማድረስ ቃል ስለገቡ በኢየሩሳሌምና በአካባቢው የሚኖሩ ተከታዮቹ ከህዝቡ ጋር ተቀላቅለው ሄዱ።



የሱስ ከጲላጦስ አደባባይ ወጥቶ በሩን እንዳለፈ ለበርባን መሰቀያ ተብሎ የተዘጋጀውን መስቀል በቆሰለውና በሚደማው ትከሻው ላይ አሸከሙት። የበርባን ጓደኞች የነበሩ ሁለት ሰዎች የሞት ፍርድ ተበይኖባቸው ስለነበር እነርሱም መስቀሎቻቸውን እንዲሸከሙ ተደረገ። አዳናችን በደረሰበት ስቃይ ምክንያት አቅም ስላነሰው የተጫነበትን ሸክም መቻል አቃተው። ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት ከበላ ወዲህ እህል ውሀ አልቀመሰም ነበር። በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ከሰይጣን ሰራዊት ጋር በነበረው ግብግብ ብዙ ተሰቃየ። አሳልፎ በተሰጠ ጊዜ እጅግ ተሰቃየ፤ ደቀ መዛሙርቱም ትተውት ሲሸሹ አየ። መጀመሪያ ወደ ሀና ቀጥሎ ወደ ቀያፋ ከዚያ በኋላ ወደ ጲላጦስ ተወሰደ። ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ ከተላከ በኋላ እንደገና ተመልሶ ወደ ጲላጦስ እንዲመጣ ተደረገ። በዚያ ሌሊት የደረሰበት እንግልት፣ ስድብ፣ ፌዝና ግርፋት የሰውን ነፍስ እስከ መጨረሻው የሚፈታተን ነበር። የሱስ አባቱን የሚያስከብር ነገር ብቻ ከመናገር ውጭ ሌላ ነገር ሳይናገር ሁሉን ነገር በዝምታ ቻለ። የደረሰበትን አሳፋሪና የሀሰት ምርመራ ሁሉ በክብርና በቁርጠኝነት ተቋቋመ። ነገር ግን ከሁለተኛው ግርፋት በኋላ መስቀሉን ባሸከሙት ጊዜ ሰብዓዊነት መቋቋም ተሳነው። ሰውነቱ ዝሎ መስቀሉን እንደተሸከመ ወደቀ።

ከኋላው ይከተሉት የነበሩት ሰዎች ደክሞት እየተንገዳገደ እንደሚሄድ እያዩ አላዘኑለትም። እንዲያውም መስቀሉን መሸከም ስላቃተው ይተናኮሉትና ይሰድቡት ነበር። ከወደቀበት አንስተው መስቀሉን ሲያሸከሙት እንደገና ተመልሶ ወደቀ። በዚህ ጊዜ ጠላቶቹ መስቀሉን ተሸክሞ መሄድ እንደማይችል ገባቸው። ይህን የሀፍረት ሸክም በማን ላይ እንደሚጭኑትም ግራ ገባቸው። ለፋሲካው በዓል የሚያረክሳቸው ስለሚሆን አይሁዳውያን መስቀሉንም መሸከም አልፈለጉም። ለአድማ ከመጡት ሰዎች መካከል እንኳ መስቀሉን በመሸከም ራሱን ለማዋረድ ፈቃደኛ የሆነ አንድም ሰው አልተገኘም።

ስምዖን የቀሬናዉ

በዚህ ጊዜ ስምዖን የተባለ አንድ የቀሬና ሰው ከገጠር ወደ ከተማ ሲሄድ የሱስን ይዘው ከሚሄዱት ሰዎች ጋር ተገናኘ። ህዝቡ ይናገሩ የነበረው የብልግና ንግግርና ለአይሁድ ንጉስ መንገድ ልቀቁለት! እያሉ በተደጋጋሚ በንቅት ስሜት ሲጮኹ ሰማ። ቆሞ በሀዘንና በመገረም ሲመለከት የየሱስ ጠላቶች ይዘው መስቀሉን አሸከሙት።



ስምዖን ደቀ መዝሙር አይሁን እንጂ ስለ የሱስ የሚያውቅ ሰው ነበር። ልጆቹ የየሱስ አማኞች ነበሩ። መስቀሉን ተሸክሞ ቀራንዮ ማድረስ ለስምዖን ትልቅ በረከት ስለሆነ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ላጋጠመው እድል ባለውለታ ሆነ። በዚህ ጥሩ አጋጣሚ ምክንያት ስምዖን የክርስቶስን መስቀል በራሱ ፍላጎት ደስ እያለው እንደተሸከመ ኖረ።

በርካታ ርኅሩኅ ሴቶች

ኃጢአት የሌለበቱ ጌታ በአሰቃቂ ሁኔታ ወደሚሞትበት ቦታ ሲሄድ ይከተሉት ከነበሩት ሰዎች መካከል ብዙ ሴቶች ነበሩ። እነዚህ ሴቶች ስለ የሱስ ያስቡ ነበር። ከእነርሱ መካከል አንዳንዶቹ ከዚያ በፊት አይተውታል፣ አንዳንዶቹ ቀደም ሲል ህሙማንን ወደ እርሱ ያመጡ ነበሩ። አንዳንዶቹም የሱስ ከደዌ የፈወሳቸው ነበሩ። በየሱስ ላይ ስለደረሰው ግፍና በደል በሰሙ ጊዜ ልባቸው የሚጨነቅለትንና የሚወዱትን ጌታ ይከተለው የነበረው ሕዝብ ለምን እንደጠላው ይገርማቸው ነበር። የተናደደው ሕዝብ የሚፈፅመውን ድርጊትና የካህናቱንና የሹማምንቱን የቁጣ ንግግር ችላ በማለት ሴቶቹ ለየሱስ የነበራቸውን ርህራሄ ከመግለፅ ወደኋላ አላሉም። የሱስ ሰውነቱ ዝሎ መስቀሉን እንደተሸከመ ሲወድቅ ባዩ ጊዜ ሃዘናቸውን በለቅሶ ዓይነት ጩኸት ገለፁ።

የየሱስን ስሜት የሳበው ይህ ብቻ ነበር። ምንም እንኳን የዓለምን ኃጢአት በመሸከሙ ምክንያት ስቃይ ቢበዛበትም ይህን ዓይነት ሀዘን ችላ ማለት አልቻለም። እነዚህን ሴቶች በርህራሄ ዓይን ተመለከታቸው። እነዚህ ሴቶች አማኝ ስላልነበሩ ያዘኑለት የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ በመሰቃየቱ ሳይሆን በሰብዓዊ የርህራሄ መንፈስ ተገፋፍተው ነው። የሱስ የእነርሱን ሀዘኔታ ችላ አላለም እንዲያውም የእነርሱ ሀዘኔታ እርሱ ለእነርሱ የበለጠ እንዲያዝንላቸው ስለ አደረገው “እናንተ የኢየሩሳሌም ሴቶች! ስለ ራሳችሁና ስለ ልጆቻችሁ አልቅሱ እንጂ ስለ እኔ አታልቅሱ” አላቸው። የሚታየው የኢየሩሳሌም መደምሰስ ነበር። አሰቃቂ የሆነው የኢየሩሳሌም መደምሰስ በደረሰ ጊዜ ኢየሱስ ያለቅሱ የነበሩት ሴቶች ከነልጆቻቸው ሲጠፉ ታዩት።



የሱስ ከኢየሩሳሌም ጥፋት ባሻገር ትልቁ የፍርድ ቀን ታየው። ንስሀ ያልገባችው የኢየሩሳሌም ከተማ ጥፋት በዓለም ላይ የሚደርሰው የመጨረሻው ጥፋት ምሳሌ ሆኖ ታየው። “በዚያ ጊዜ ሰዎች ተራራዎችን በላያችን ውደቁ! ኮረብቶችንም ሸሽጉን! ማለት ይጀምራሉ። እንግዲህ ይህ ሁሉ ነገር በእርጥብ እንጨት ላይ የሚደረግ ከሆነ በደረቅ እንጨት ላይማ ምን ይደረግ ይሆን?” አለ። እርጥብ እንጨት ሲል ምንም እንከን የማይገኝበትን የዓለም አዳኝ የሆነውን ራሱን ማለቱ ነው። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን ቁጣ በተወዳጁ ልጅ ላይ አወረደው። የሱስ ስለ ሰዎች ኃጢአት መሰቀል ነበረበት። ኃጢአትን በመስራት የሚቀጥል ሰው ምን ዓይነት ስቃይ ይደርስበት ይሆን? ንስሀ የማይገቡና የማያምኑ ሁሉ በቅንቋ ሊገለፅ የማይቻል ሀዘንና ስቃይ እንደሚደርስባቸው ያውቃሉ።

ከሆሳዕና እስከ “ስቀለው”

አዳኛችን ለመሰቀል ወደ ቀራንዮ ሲሄድ ከተከተሉት ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ በአህያ ላይ ተቀምጦ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ የዘምባባ ዝንጣፊ እያውለበለቡና የደስታ መዝሙር እየዘመሩ ያጀቡት ናቸው። ያን ጊዜ ሰዎች ያደረጉትን ተከትለው የውዳሴ መዝሙር የዘመሩለት አንዳንድ ሰዎች በዚያው አንደበታቸው “ስቀለው! ስቀለው!” የሚል ጩኸት አብረው አስተጋቡ። የሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በገባበት ወቅት የደቀ መዛሙርቱ ተስፋ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነበር። በዚያን ጊዜ ወደ እርሱ መቅረብ ክብር ስለመሰላቸው ወደ እርሱ በጣም ተጠጉ። አሁን ግን ውርደት በደረሰበት ጊዜ ከሩቅ ተከተሉት። እያዘኑ ተስፋ በመቁረጥ አንገታቸውን ደፉ። የሱስ “እረኛውን መትቼ እገድላለሁ፣ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ ተብሎ ተፅፎአልና በዚህች ሌሊት ሁላችሁም ትክዱኛላችሁ፣” ሲል የተናገረው ተረጋገጠ (ማቴ. 26፡31)።



ማርያም፤ ከግርግም እስከ ቀራንዮ

ከመሰቀያው ቦታ በደረሱ ጊዜ እስረኞቹ ለማሰቃያ በተዘጋጀው መሳሪያ ላይ ታሰሩ። ሁለቱ እስረኞች በመስቀል ላይ ላለመታሰር ታገሉ የሱስ ግን ምንም የመከላከል ሙከራ አላደረገም። የየሱስ እናት በተወዳጁ ደቀ መዝሙር በዮሐንስ እየተረዳች ልጅዋን እስከ ቀራንዮ ተከተለችው። የሱስ ሰውነቱ ዝሎ መስቀሉን እንደተሸከመ ሲወድቅ ስላየችው የቆሰለውን ራሱን በእጆችዋ ደገፍ ልታደርግለትና በህፃንነቱ ደረትዋን ይጉተራስ የነበረውን ግንባር ልታጥብለት ብትችል ደስ ባላት ነበር። ነገር ግን ይህን የማድረግ ዕድል አላገኘችም። እርስዋ እንደ ደቀ መዘሙርቱ የሱስ ኃይሉን በመጠቀም ራሱን ከጠላቶቹ እጅ ያድናል የሚል ተስፋ ነበራት። ቢሆንም አሁን ስለደረሰበት ሁኔታ አስቀድሞ የተናገረውን ባስታወሰች ቁጥር ልብዋ ይሸበርባት ነበር። ሁለቱ ሌቦች በመስቀል ላይ ሲታሰሩ ባየች ጊዜ ለሙታን ህይወትን የሰጠ ጌታ ራሱን ለስቅላት አሳልፎ ይሰጥ ይሆን? እያለች በጭንቀት ትጠባበቅ ነበር። የእግዚአብሔር ልጅ በጭካኔ ለመገደል ራሱን አሳልፎ ይሰጥ ይሆን? አለች። ስለ የሱስ መሲህነት የነበራትን እምነት መተው ይኖርባት ይሆን? በደረሰበት ችግር እርዳታ የመስጠት እድል ባይኖራት የደረሰበትን ሀፍረትና ሀዘን ዝም ብላ ትመልከት? የየሱስ እጆች በመስቀሉ ላይ ተዘርግተው በምስማር ሲቸነከሩና ምስማሮቹ ለስላሳ ስጋውን በስተው ሲገቡ በማየታቸው እጅግ ያዘኑት ደቀ መዘሙርቱ ራስዋን የሳተችውን የየሱስን እናት ከዚያ ዘግናኝ ትእይንት ለማራቅ ተሸከመው ወሰዷት።



የሚያደርጉትን አያውቁምና ...

አዳኛችን የማጉረምረም ወይም የቅሬታ ድምፅ አላሰማም። በፊቱ ላይ እርጋታና ፍፁም ሰላም ሲታይበት በግንባሩ ላይ ትልልቅ የላብ ጠብታዎች ይታዩ ነበር። በዚያ ወቅት በግንባሩ ላይ የነበረውን ላብ የሚጠርግለት ወይም ሰብዓዊ ልቡን ለማረጋጋት በታማኝነት ከጎኑ ቆሞ የሚያፅናናው ሰው አልተገኘም። ወታደሮቹ ያን ሁሉ አሰቃቂ ድርጊት እየፈፀሙበት ሳለ የሱስ "አባት ሆይ! የሚያደርጉትን ስለማያውቁ ይቅር በላቸው!" በማለት ለጠላቶቹ ፀለየላቸው። የሱስ የራሱን ስቃይ ችላ ብሎ ስለ አሳዳጆቹ ኃጢአትና ስለሚደርስባቸውም ቅጣት ተጨነቀ። የጭካኔ ድርጊት የፈፀሙትን ወታደሮች አልረገማቸውም። እቅዳቸው ስለተሳካላቸው በየሱስ መሲቃየት በተደሰቱት ካህናትና ሹማምንት ላይ የበቀል እርምጃ እንዲወሰድባቸው አልጠየቀም። በዚህ ፈንታ ስለ ድንቁርናቸውና ኃጢአታቸው አዘነላቸው። "የሚያደርጉትን ስለማያውቁ ይቅር በላቸው!" ብሎ ፀለየላቸው።



እነዚያ ሰዎች እንዲያ የሚያሰቃዩት የጠፋውን ሰብዓዊ ዘር ከዘላለም ጥፋት ለማዳን የመጣውን ጌታ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ ጸጸትና ድንጋጤ ይይዛቸው ነበር። ነገር ግን የሱስ አዳኛቸው መሆኑን አውቀው የመቀበል እድል ስለነበራቸው አለማወቃቸው ከኃጢአተኛነት ነፃ ሊደርጋቸው አልቻለም። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ኃጢአታቸውን አውቀው ንስሃ የሚገቡና የሚመለሱ ነበሩ። አንዳንዶቹ ንስሃ ባለመግባታቸው ምክንያት የሱስ ስለ እነርሱ ያቀረበው ፀሎት መልስ እንዳያገኝ አደረጉ። ያም ሆነ ይህ በዚያ ወቅት የእግዚአብሔር እቅድ በመፈፀም ላይ ነበር። የሱስም በአባቱ ፊት የሰው ዘር ጠበቃ የመሆን መብቱን እያስከበረ ነበር።

በዚያን ጊዜ የሱስ ለጠላቶቹ የፀለየው ፀሎት ዓለምአቀፋዊ ነው። ያ ፀሎት ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጊዜ ፍፃሜ ድረስ የኖረውን ወይም የሚኖረውን ማንኛውንም ኃጢአተኛ ይመለከታል። እያንዳንዱ ሰው የሱስን

የመስቀል ወንጀል ይመለከተዋል። እንደዚሁም እያንዳንዱ ሰው ይቅርታ ተደርጎለታል። የሚፈልግ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅና የዘላለም ህይወት ወራሽ መሆን ይችላል።

"የናዝሬቱ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ"

የሱስ በመስቀሉ ላይ በምስማር እንደተቸነከረ መስቀሉ በጠንካራ ሰዎች ተነስቶ በተዘጋጀለት ቦታ ላይ በኃይል ተተከለ። ይህ በሚደረግበት ጊዜ በየሱስ ላይ ትልቅ ስቃይ አደረሰበት። ጲላጦስ በፅበራይስጥ፣ በላቲንና በግሪክ የተፃፈ ማስታወቂያ በክርስቶስ ራስጌ በመስቀሉ ላይ አኖረ። ማስታወቂያው "የናዝሬቱ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ" የሚል ሲሆን ስያሜው አይሁዶችን አስቆጣቸው። አይሁዶች ቀደም ሲል በጲላጦስ አደባባይ "ስቀለው!" "ከቄሳር በቀር ሌላ ንጉስ የለንም" ሲሉ ጮኸው ነበር (ዮሐ.. 19፡15)። ሌላ ንጉስ ለመኖሩ እውቅና የሚሰጥ ሁሉ ከዳተኛ ነው ሲሉ አበክረው ተናገሩ። ጲላጦስ የፃፈው በስሜታቸው የገለፀትን ነበር። እነርሱ የአይሁድ ንጉሥ ከሚለው በስተቀር ሌላ ተቃውሞ አልነበራቸውም። ይህ ማስታወቂያ አይሁዶች ለሮም መንግስት ታማኝ የመሆናቸው ማረጋገጫ ነበር። ይህ ማስታወቂያ የአይሁድ ንጉሥ ነኝ ብሎ የሚነሳውን ማንኛውንም ሰው አይሁዶች የሞት ፍርድ እንደሚፈርዱበት ያረጋግጣል። ካህናቱ ሳያውቁት ወሰናቸውን አለፉ። የሱስን ለመግደል በሚያሴሩበት ጊዜ ቀያፋ ህዝቡን ለማዳን አንድ ሰው ቢሞት የተሻለ ነው ሲል ተናግሮ ነበር። ታዲያ አሁን ግብዝነታቸው ተጋለጠ። ክርስቶስን ለማጥፋት ሲሉ የማንነታቸውን ህልውና ከአደጋ ላይ ለመጣል ዝግጁ ሆኑ።



ካህናቱ የሰሩት ነገር ወደ ምን እንደሚያመራ በገባቸው ጊዜ ማስታወቂያውን እንዲቀይር ጲላጦስን ጠየቁት። "አንተ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትፃፍ፣ ነገር ግን ይህ ሰው እኔ የአይሁድ ንጉሥ ነኝ ብሎአል ብለህ ፃፍ፣" አሉት። ጲላጦስ ግን ቀደም ሲል ባሳየው ድክመት ተናድዶ ስለነበርና ካህናቱንና ሹማምቱን በቀናተኝነታቸውና በተንኮላቸው ምክንያት ንቆአቸው ስለነበር በግድ የለሽነት "የፃፍሁትን ፅፌአለሁ፣" ሲል መለሰላቸው።

ያ ማስታወቂያ እንደዚያ ተፅፎ እንዲሰቀል ያደረገ ከአይሁዶችና ከጲላጦስ በላይ የሆነ አንድ ኃይል ነበር። በእግዚአብሔር ፀጋ ይህ ማስታወቂያ ሰዎች ቅዱሳት መፃህፍትን እንዲመረምሩ ለማድረግ አሳባቸውን የሚቀሰቅስ ነበር። የሱስ የተሰቀለበት ቦታ ለኢየሩሳሌም ቅርብ ስለነበር ከልዩ ልዩ ቦታ ወደ ከተማው መጥተው የነበሩትን ሰዎች ማስታወቂያው ስለ የሱስ መሲህነት እንዲያስታውሱ አደረጋቸው። ስለዚህ ይህ ማስታወቂያ እግዚአብሔር በመራው እጅ የተፃፈ ህያው እውነት ነበር።

ትንቢቱና ፍጻሜው

የሱስ በመስቀል ላይ የተሰቃየው አስቀድሞ በተነገረ ትንቢት መሠረት ነው። ከመሰቀሉ ብዙ ምዕተ ዓመታት አስቀድሞ አዳኛችን ስለሚደርስበት ችግር ትንቢት ተናግሮ ነበር። "ክፉ ሰዎች እንደ ውሻ መንጋ ከበቡኝ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩ። አጥንቶቼ ተቆጠሩ፣ ጠላቶቼም በጥላቻ አይን ተመለከቱኝ። ልብሶቼን ተከፋፈሉ፣ በእጅ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፣" ሲል ተናግሮ ነበር (መዝ. 22፡16-18)። ስለ ልብሱ የተነገረው ትንቢት ከየሱስ ጠላቶች ወይም ወዳጆች የተሰጠ አንድም መመሪያ ወይም ጣልቃገብነት ሳይኖር ተፈፀመ። የየሱስ ልብስ በመስቀል ላይ ለሰቀሉት ወታደሮች ተሰጠ። ወታደሮቹ ልብሱን በሚከፋፈሉበት ጊዜ በመካከላቸው የነበረውን ጭቅጭቅ የሱስ ይሰማ ነበር። "እጅ ጠባቡ ሳይሰፋ ከላይ እስከታች ወጥ ሆኖ የተሰራ፣" ስለነበር "ለማን እንደሚደርስ ለማወቅ ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ።"

በሌላ ትንቢት አዳኛችን "ስድብ ልቤን ስለሰበረው ተስፋ ቆረጥሁ፣ የሚያስተዛዝነኝ ሰው ፈለግሁ ነገር ግን ማንም አልነበረም። የሚያፅናናኝ ሰው ፈለግሁ ነገር ግን ማንም አልተገኘም። በምግቤ ውስጥ መራራ ነገር ቀላቀሉ፣ በጠማኝም ጊዜ በውህ ፈንታ ሆምጣጤ ሰጡኝ" ሲል ተናግሮ ነበር (መዝ. 69፡20-21)። በመስቀል ላይ የስቃይ ሞት ለሚሞቱ ሰዎች የህመሙን ስሜት ለመቀነስ ሲባል የሚያደነዝዝ መድኃኒት መስጠት ይፈቀድ ነበር። ይህ ለየሱስ ቀርቦለት ነበር ነገር ግን አእምሮውን የሚያደነዝዝ ነገር መውሰድ ስላልፈለገ ቀምሶ ተወው።

በእምነት እግዚአብሔርን መጠማጠም ነበረበት። የኃይሉ ምንጭ ይህ ብቻ ነበር። ህሊናውን ቢያደነዝዝ ኖሮ ለሰይጣን ጥቃት ይመቻቸ ነበር።

"የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ ..."

የሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ ጠላቶቹ ቁጣቸውን ገለፁ። ለመሞት በማጣጣር ላይ በነበረው ጌታችን ላይ ካህናት፣ ሹማምንትና ፀሀፍት ከአድመኛው ሕዝብ ጋር ተባብረው አፌዙበት።

የሱስ በተጠመቀና በተራራ ላይ በተለወጠ ጊዜ ክርስቶስ ልጁ መሆኑን በመግለፅ እግዚአብሔር ተናግሮ ነበር። እንደዚሁም የሱስ አሳልፎ ከመሰጠቱ በፊት እግዚአብሔር አብ የየሱስ መለኮታዊነት ማስረጃ የሆነውን ድምፁን አሰምቶ ነበር። አሁን ግን ከሰማይ ምንም ድምፅ አልተሰማም። ስለ የሱስ የተሰማ ምስክርነትም አልነበረም።



ክፉ ሰዎች ያደረሱበትን መከራና ፌዝ ብቻውን ተጋፈጠ።

"የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እስቲ ከመስቀል ውረድ" "እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው መሲህ ከሆነ እስቲ ራሱን ያድን፣" እያሉ አላገጡበት። የሱስ በምድረ በዳ በተፈተነ ጊዜ ሰይጣን "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እስቲ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ"፤ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እስቲ ከዚህ (ከቤተ መቅደስ ጣራ) ወደታች ዘለህ ውረድ፣" ብሎ ነበር። ማቴ. 4፡3፣6። የሱስ በተሰቀለ ጊዜ ሰይጣንና መላእክቱ ሰው መስለው ከዚያ ነበሩ። ቀንደኛው ጠላትና ሰራዊቱ የካህናቱና የሹማምንቱ ተባባሪ ነበሩ። የህዝቡ መምህራን ምንም የማያውቁትን ተራ ሰዎች እንዲያውም ብዙዎቹ በሀሰት ለመመስከር እስከተጠሩበት ጊዜ ድረስ አይተውት በማያውቁት በየሱስ ላይ እንዲፈርዱ አነሳሱዋቸው። ካህናቱ፣ ሹማምንቱ፣ ፈሪሳውያንና ተራው ሕዝብ በሰይጣናዊ እብደት አንድ ግንባር ፈጠሩ። የሀይማኖት መሪዎች ከሰይጣንና ከመላእክቱ ጋር ተዋሀዱ፣ የእርሱ ትእዛዝ ፈጻሚም ሆኑ።

የሱስ እየተሰቃየ በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ካህናቱ "ሌሎችን አዳነ ራሱን ግን ማዳን አይችልም። እርሱ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ እስቲ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም እንመንበት፣" ብለው የተናገሩትን እያንዳንዱን ቃል ሰማ። ክርስቶስ ከመስቀል መውረድ ይችል ነበር። ነገር ግን ኃጥአን በእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታንና ተተቀባይነትን ያገኙት እርሱ ራሱን ማዳን ስላልፈለገ ነው።

የትንቢት ተርጓሚዎች የተባሉት ሰዎች በአዳኛች ላይ ባፌዙበት ጊዜ ይህን ነገር እንደሚያደርጉ መንፈስ አስቀድሞ የተናረውን ቃል መደጋገማቸው ነበር። ይሁን እንጂ ህሊናቸው ስለታወረ በትንቢት የተነገረውን እየፈፀሙ መሆኑ አልታያቸውም። በማፌዝ "እሱ በእግዚአብሔር ታምኖአል የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሚወደው ከሆነ እስቲ አሁን ያድነው፣" ብለው የተናገሩት የምስክርነት ቃል ለዘመናት ሁሉ ሲነገር እንደሚኖር አላወቁም። እነዚህ ቃላት የተነገሩት ለፌዝ ቢሆንም ሰዎችን ከቀድሞው የበለጠ ቅዱሳት መፃህፍትን እንዲመረምሩ አድርገዋቸዋል። አስተዋይ ሰዎች አዳመጡ፣ መረመሩ፣ በጥልቀት አሰቡ፣ ፀለዩም። የክርስቶስን ተልዕኮ ምንነት እስኪረዱ ድረስ ጥቅስን ከጥቅስ እያወዳደሩ በማጥናት እረፍት የሌላቸው ሰዎች ተነሱ። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሰቀሉ ምክንያት ሰዎች ከዚያ በፊት ስለ እርሱ ካወቁት የበለጠ አጠቃላይ እውቀት አገኙ። ስቅለቱን ላዩና እርሱ የተናገረውን ለሰሙ ብዙ ሰዎች የእውነት ብርሀን በራላቸው።

"አቤቱ አስበኝ"

የሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ በሚሰቃይበት ወቅት አንድ የሚያፅናናው ነገር ተገኘ። ይህም ንስሀ የገባው ሌባ የፀለየው ፀሎት ነው። ከየሱስ ጋር የተሰቀሉት ሁለት ሰዎች መጀመሪያ የሱስን ይሰድቡትና ያፌዙበት ነበር፤ በተለይ አንደኛው ከስቃዩ የተነሳ ተስፋ የቆረጠና እልኸኛ ነበር። ሁለተኛው ግን ከዚያ የተለየ ነበር። ይህ ሰው ልቡ የደነደነ ወንጀለኛ ሳይሆን በመጥፎ ጓደኞች ተመርቶ ወንጀል የሰራና በመስቀሉ ዙሪያ ቆመው የሱስን ይሰድቡ ከነበሩት ሰዎች ከአብዛኛዎቹ የተሻለ ወንጀለኛ ነበር። ሰውዬው ቀደም ሲል የሱስን የሚያውቅና

ትምህርቱን አምኖ የተቀበለ ነበር፣ ነገር ግን በካህናቱና ሹማምንቱ ተፅዕኖ ከየሱስ እንዲርቅ ተደረገ። የህሊና ወቀሳውን ለማጥፋት ሲል ቀስ በቀስ ወደ ኃጢአት ማጥ ስለገባ በወንጀለኛነት ተያዘ፣ ወንጀለኛነቱ በምርመራ ስለተረጋገጠበት በስቅላት እንዲሞት ተፈረደበት። ይህ ሰው በፍርድ ቤቱ አዳራሽና ወደ ቀራንዮ በተደረገው ጉዞ ከየሱስ ጋር ነበር። ጲላጦስ “እነሆ ምንም በደል እንዳላገኙበት እንድታውቁ፣” ብሎ የተናገረውን ሰምቷል (ዮሐ. 19፡4)። ይህ ወንጀለኛ የየሱስን አምላካዊ ባህርይ ልብ ብሎ ተመልክቷል፣ የሚያሰቃዩትን ሰዎች በርህራሄ መንፈስ ይቅርታ ሲያደርግላቸውም አይቷል።



በመስቀል ላይ ሆኖ ትልልቅ የህይማኖት ሊቃውንት ጌታ የሱስን ለማዋረድ አፋቸውን ለስድብ ሲከፍቱ አይቷቸዋል። ራሳቸውን ሲነቀንቁበትም ተመልክቷል። የወንጀል ተባባሪ ጓደኛው “አንተ መሲህ አይደለህምን? እስቲ በል ራስህንና እኛን አድን!” እያለ ሲዘልፈው ሰማ። አልፎ ሂያጆች የሱስን በመደገፍ ሲናገሩ አዳመጠ። የሱስ የተናገረውን እየጠቀሱ ሲያወሩና ስለ ፈፀማቸው ድርጊቶች ሲናገሩ ሰማ። በዚህ ጊዜ ቀደም ሲል በየሱስ መሲህነት ያመነው ትውስ አለውና ወደ ወንጀለኛ ባልደረባው ዘወር ብሎ “አንተ ደግሞ በሞት ፍርድ ላይ እያለህ እንኳ እግዚአብሔርን አትፍራምን?” አለው። እነዚህ በሞት አፋፍ ላይ ያሉ ሌቦች በዚያ ጊዜ ሰውን የሚፈሩት ምንም ምክንያት አልነበረም። ቢሆንም ከሁለቱ ወንጀለኞች አንዱ ሊፈሩት የሚገባ አምላክ እንዳለና የሚያስደነግጥ ጊዜ እንደሚመጣ አመነ። በኃጢአት እንደተበከለ የዚህ ሰው የህይወት ታሪክ ወደ ፍፃሜ ለመድረስ ተቃርቦ ነበር። “እኛ ባደረግነው በደል ምክንያት ቅጣት መቀበላችን የተገባ ፍርድ ነው። ይህ ሰው ግን ምንም ጥፋት አላደረገም፣” ሲል እያቃሰተ ተናገረ።

አሁን ጥያቄ፣ ጥርጣሬና ሀፍረት ሁሉ ጠፋ። ይህ ሌባ በወንጀሉ ምክንያት የሞት ፍርድ በተበየነበት ጊዜ ተስፋ ቆርጦ ነበር፣ አሁን ግን አዲስና ጥሩ አስተሳሰብ በውስጡ ማንሰራራት ጀመረ። የሱስ ህሙማንን እንደፈወሰና ኃጢአትን ይቅር እንዳለ የተናገረው ሁሉ አንድ በአንድ ትዝ ይለው ጀመር። በየሱስ የሚያምኑ ሰዎች እያለቀሱ በሚከተሉት ጊዜ ይናገሩ የነበረውን ሰምቶ ነበር። በየሱስ ራስጌ የተሰቀለውን ማስታወቂያ አንብቦ ነበር። ከአልፎ ሂያጆች መካከል አንዳንዶቹ ማስታወቂያውን በህዘንና በፍርሀት አንዳንዶቹ ደግሞ በንቀትና በፌዝ ሲያነብቡ አይቷል። መንፈስ ቅዱስ ኅሊናውን ብሩህ ስላደረገለት ስለ የሱስ ማንነት መረጃዎች ቀስ በቀስ ተያያዙለት። በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሰውነቱ የቆሳሰለውና መሳቂያና መሳለቂያ የሆነው የሱስ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ መሆኑን አወቀ። ይህ አቅመቢስ የሆነና በሞት አፋፍ ላይ የነበረ ሰው በሞት አፋፍ ላይ ለነበረ አዳኝ ራሱን በሰጠ ጊዜ የተስፋና የሰቃይ ስሜት በተቀላቀለበት አንደበት “አስበኝ አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ፣” ሲል ጮኸ። መልሱን ወዲያው አገኘ። ፍቅር፣ ርህራሄና ኃይል በተሞላበት፣ በለሰለሰና ጣዕመ ዜማ ባለው አነጋገር አዳኛችን “እውነት እልሀለሁ ዛሬ፣ ከእኔ ጋር በገነት እንድትሆን፣” ሲል አረጋገጠለት።

የአይሁድ መሪዎች በናቁትና ደቀ መዛሙርቱ እንኳ መለኮታዊነቱን በተጠራጠሩት ሰዓት ለዘላለማዊ ህይወት የተዘጋጀ አንድ ምስኪን ሌባ የሱስን ‘ጌታ!’ ብሎ ጠራው።

የሱስ ለረጅም ጊዜ እየተሰቃየ ይሰማ የነበረው ስድብና ፌዝ ብቻ ነበር። በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ ከፌዝና ከእርግማን ሌላ የሚሰማው ነገር አልነበረም። ከደቀመዛሙርቱ የእምነት መግለጫ ድምፅ ለመስማት ጓጉቶ ነበር ነገር ግን በዚህ ፈንታ የሰማው “እኛ ግን እስራኤልን የሚያድን እርሱ ነው ብለን ተስፋ አድርገን ነበር” የሚል የሀዘን እንጉርጉሮ ብቻ ነው። ጌታችን በሞት አፋፍ ላይ ከነበረ አንድ ሌባ የእምነትና የፍቅር መግለጫ ንግግር መስማቱ ምን ያህል አስደስቶት ይሆን! የአይሁድ መሪዎች በናቁትና ደቀ መዛሙርቱ እንኳ መለኮታዊነቱን በተጠራጠሩት ሰዓት ለዘላለማዊ ህይወት የተዘጋጀ አንድ ምስኪን ሌባ የሱስን ጌታ ብሎ ጠራው። የሱስ ተአምራት በሥራ ጊዜና ከሞት ከተነሳ በኋላ ብዙዎች ጌታ ሊሉት ዝግጁ ነበሩ ነገር ግን በመስቀል ላይ ተቸንክሮ ሊሞት በተቃረበበት ሰዓት ከህይወቱ በመጨረሻዋ ደቂቃ አካባቢ ንስሀ ገብቶ ከዳነው ሌባ በስተቀር ጌታ ብሎ የጠራው ማንም የለም።

በመስቀሉ አጠገብ የቆሙ ሰዎች ሌባው የሱስን ጌታ ሲለው ሰሙት። ንስሀ የገባው ሰውዬ አነጋገር ትኩረታቸውን ሳበው። በመስቀሉ ግርጌ ሆነው ስለ ክርስቶስ ልብስ ይጨቃጨቁና እጣ ይጣጣሉ የነበሩም ጩኸታቸውን አቁመው አዳመጡ። የቁጣ ንግግራቸውን ጋብ አድርገው ከየሱስ አንደበት የሚወጣውን መልስ ለመስማት አፋቸውን ከፍተው ተጠባበቁ።

የሱስ ለሰውዬው የዘላለም ህይወት ተስፋ በሰጠው ጊዜ መስቀሉን እንደመሸፈን አድርጎት የነበረውን ዳመና ዘልቆ የመጣ ብሩህ ብርሀን ታየ። ንስሃ የገባው ሌባ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘ ፍፁም ሰላም አገኘ። ክርስቶስም በውርደቱ መካከል ክብር አገኘ። በሰው ዘንድ የተሸነፈ የመሰለው ጌታ አሸናፊ ሆነ፣ ኃጢአት ተሸካሚ መሆኑም ታወቀ። ሰዎች በስጋዊ አካሉ ላይ ኃይላቸውን ማሳየት፣ በሾህ አክሊል ጆሮ ግንዱን መውጋት፣ ልብሱን ገፍፈው ስለ ልብሱ መጨቃጨቅ ይችላሉ ነገር ግን ለኃጢአት ይቅርታ የመስጠት ኃይሉን ሊነጥቁት አልቻሉም። በሞቱ ስለ መለኮታዊነቱና ስለ እግዚአብሔር ክብር መሰከረ። ጆሮው ቶሎ የማይሰማ፣ እጁም ለመፈወስ ያጠረ አይደለም። በእርሱ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሁሉ ፈፅሞ ለማዳን መለኮታዊ ስልጣን አለው።

“እውነት እልሀለሁ ዛሬ፤ ከኔ ጋር በገነት እንድትሆን።” ክርስቶስ ንስሀ ለገባው ሌባ በዚያው ቀን ይዞት ገነት እንደሚገባ ተስፋ አልሰጠውም ምክንያቱም የሱስ ራሱ በዚያ ቀን ወደ ገነት አልሄደምና። በመቃብር ውስጥ ከቆየ በኋላ በትንሳኤ ዕለት ጥዋት “ገና ወደ አባቴ አልወጣሁምና፣” ሲል ተናግሯል (ዮሐ. 20፡17)። ነገር ግን ሽንፈትና ጨለማ የሰፈነበት በመሰለው የስቅለት ቀን ለሰውዬው ወደ ገነት የመግባት ተስፋ ተሰጠው። የሱስ እንደ ወንጀለኛ በተሰቀለበት ቀን ንስሀ ለገባው ወንጀለኛ “ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ!” ሲል አረጋገጠለት።



ከፍተኛው ወንጀለኛ

“ከኢየሱስ ጋር ሁለት ወንበዴዎችን አምጥተው አንዱን በቀኙ አንዱንም በግራው” እርሱን በመካከል አድርገው ሰቀሉ። ይህ እንዲሆን መመሪያ የሰጡ ካህናቱና ሹማምንቱ ናቸው። ክርስቶስ በመካከል ሆኖ እንዲሰቀል የተደረገበት ምክንያት ከሶስቱ ከፍተኛው ወንጀለኛ እርሱ መሆኑን ለማሳወቅ ነው። ይህ በመሆኑ “ከክፉ አድራጊዎችም ጋር ተቆጥሮአል፣” የሚለው ትንቢት ተፈፀመ (ኢሳ. 53፡12)። ካህናቱ የድርጊታቸው ትክክለኛ ትርጉም አልገባቸውም። የሱስ ከሌቦች መካከል መሰቀሉ የሚያመለክተው መስቀሉ በኃጢአት በጠፋ ዓለም መካከል የተተከለ መሆኑን ነው። በዚህ መስቀል ላይ ንስሀ ለገባው ሌባ የተነገረው የኃጢአት ይቅርታ በዓለም ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የሚያበራ የተስፋ ብርሀን ፈነጠቀ።

የሱስ ከፍተኛ የህሊናና የአካል ጭንቀት በሚያሰቃየው ወቅት ራሱን ችላ ብሎ ለሌሎች ብቻ በማሰብ ያን ሌባ እንዲያምን ሲያደፋፍረው ባዩ ጊዜ መላእክት የፍቅሩ ወሰን የለሽነት አስገረማቸው። ያ ሁሉ ውርደት በደረሰበት ወቅት የሱስ ነቢይ እንደመሆኑ መጠን ለኢየሩሳሌም ሴቶች ትንቢት ተናገረ፤ ካህንና ጠበቃ እንደመሆኑም የእርሱን ገዳዮች አባቱ ይቅርታ እንዲያደርግላቸው ተማፀነ፤ አፍቃሪ አዳኝ በመሆኑም ንስሀ የገባውን ወንጀለኛ ኃጢአቱን ይቅር አለለት።

“እናቴ ሆይ! እነሆ ልጅሽ!”

የሱስ በዙሪያው የነበረውን ሕዝብ በዓይኑ ሲቃኝ ሀሳቡ በአንድ ሰው ላይ አረፈ። በመስቀሉ አጠገብ እናቱ በዮሐንስ ተደግፋ ቆማ አየ። ማርያም ከልጅዋ ተለይታ መቆየት ስላልቻለች ዮሐንስም የሱስ በህይወት ብዙ እንደማይቆይ ስላወቀ ወደ መስቀሉ መልሶ አመጣት። የሱስ በሞት አፋፍ ላይ እያለ እናቱን አስታወሰ። በሀዘን የተሳቆለውን የእናቱን ፊትና ዮሀንስን እየተመለከተ እናቱን “እናቴ ሆይ! እነሆ ልጅሽ!” አላት፤ ዮሐንስንም “ይህችውልህ እናትህ!” አለው። ዮሐንስ የሱስ የተናገረው በትክክል ስለገባው አደራውን ተቀበለ። ወዲያውኑ ማርያምን ወደ ቤቱ ወስዶ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ልዩ እንክብካቤ አደረገላት። አዛኙና አፍቃሪው አዳኛችን በዚያ የአካልና የህሊና ስቃይ መካከል ለእናቱ ተጨነቀ። የሱስ ለእናቱ እንክብካቤ የሚሆን ገንዘብ አላዘጋጀላትም ነገር ግን እርሱ በዮሐንስ ልብ ላይ የተቀረፀ ስለሆነ ለዮሐንስ እናቱን እንደተከበረ የመታሰቢያ ቅርስ አድርጎ

አስረከበው። እናቱ እርሱን ስለወደደችው የሚወዳትና የሚራራላት ሰው አዘጋጀላት። ዮሐንስም እርስዋን እንደተቀደሰ አደራ አድርጎ በመቀበሉ ትልቅ በረከት አገኘ። ማርያም ለዮሐንስ የተወደደ ጌታው የዘመትር ማስታወሻ ሆነችለት።

የሱስ ለእናቱ ያሳየው ፍፁም የሆነ ፍቅር በምሳሌነቱ የዘመናት ጭጋግ ሳይከልለው እንደ ንፁህ ሉል ሲያንፀባርቅ ኖረ። የሱስ ለሰላሳ ዓመታት ያህል የጉልበት ስራ እየሰራ የቤተሰብን ኃላፊነት ለመወጣት አስተዋፅኦ አድርጓል። አሁን ደግሞ በመሰቃየት ላይ እያለ ላዘኑትውና ባልዋ ለሞተባት እናቱ መንከባከቢያ ማዘጋጀት እንዳለበት አልረሳም። እያንዳንዱ የጌታ ደቀ መዝሙር ይህ ዓይነት መንፈስ ሊኖረው ይገባል። የክርስቶስ ተከታይ የሆኑ ሁሉ ወላጆቻቸውን ማክበርና ለወላጆቻቸው መጠንቀቅ እንዳለባቸው ከሀይማኖታቸው የሚጠበቅ ተግባር መሆኑን ማወቅ አለባቸው። አባትና እናት የክርስቶስ ፍቅር ከነገሠበት ልብ ጥንቃቄና ርህራሄ አይነፈጋቸውም።

መድኃኒዓለም፤ ቤዛና መድኅን

የክብር አምላክ የሆነው የሱስ ለሰብዓዊ ዘር ቤዛ ሆኖ የሚሞትበት ሰዓት ተቃረበ። ውድ ህይወቱን አሳልፎ በመስጠቱ የሱስ በድል አድራጊነት ደስታ አልተኩራራም። ሁሉም ነገር ተሰፋ አስቆራጭ ሆነበት። ከባድ ሸክም የሆነበት የመሞት ፍርሀት አይደለም። በአንደበት ሊገለፅ የማይቻል ስቃይ ያመጣበት ህመም የመስቀል ውርደት አልነበረም። በዓለም ላይ እንደ የሱስ የተሰቃየ ማንም የለም። ለስቃዩ ዋና ምክንያት የሆነው ግን ለኃጢአት የነበረው የጥላቻ ስሜትና ሰዎች ኃጢአትን በመለማመድ የኃጢአትን ግዙፍነት ለማየት ዓይናቸው መታወሩን ማወቁ ነው። ኃጢአት የሰውን ልብ ምን ያህል አጥብቆ እንደያዘና ከኃጢአት ኃይል ነፃ ለመውጣት ፈቃደኛ የሚሆኑ ሰዎች ምን ያህል ጥቂት እንደሆኑ ግልፅ ሆኖ ታየው። ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ሰብዓዊ ዘር ሁሉ እንደሚጠፋ አወቀ፤ በቂ እርዳታ ማግኘት ሲችሉ ብዙ ሰዎች እንደሚጠፉም ታየው።



የሱስ የእኛ ቤዛና መድኅን ስለሆነ ኃጢአታችንን ተሸከመ። እኛን ከህግ ቅጣት ለማዳን ሲል እንደ ህግ ተላላፊ ተቆጠረ። የአዳም ዘር ሁሉ ኃጢአት ልቡን አስጨነቀው። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለው ቁጣና በአመጽ ምክንያት የሚሰማው ቅፌታ የልጁን ነፍስ አስጨነቃት። ከርስቶስ መላ ህይወቱን ስለ አባቱ የመሀሪነትና የይቅር ባይነት መልካም ታሪክ ለወደቀው ዓለም ሲያበስር ኖረ። የብስራቱ ርዕስ መዳን ከኃጢአተኛ ሁሉ ለባሰ ኃጢአተኛ የሚል ነው። አሁን ግን በላዩ ላይ ባረፈው የኃጢአት ሸክም ምክንያት የአባቱን ይቅር ባይ ፊት ማየት አልቻለም። የመረረ ስቃይ በደረሰበት ወቅት የአባቱ መለኮታዊ ገፅታ ከእርሱ በመራቁ የአዳኛችን ልብ በሀዘን ምን ያህል እንደተጎዳ ሰው ሙሉ በሙሉ ሊረዳው አይችልም። በዚህ ምክንያት የደረሰበት ስቃይ እጅግ የከፋ ከመሆኑ የተነሳ በሥጋዊ አካሉ ላይ የደረሰው ጉዳት እንዳልተሰማው ይቆጠራል።

ሰይጣን በከባድ ፈተና የሱስን ልብ አስጨነቀው። አዳኛችን ከመቃብሩ በር አሻግሮ ማየት ተሳነው። ከመቃብር በአሸናፊነት እንደሚነሳና የሚከፍለው መስዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሚያገኝ ተስፋ ማድረግ ተሳነው። ኃጢአት እጅግ አስከፊ ከመሆኑ የተነሳ እርሱና አባቱ ለዘላለም ተለያይተው የሚቀሩ መሰለው። በዚህ ጊዜ የሱስ ይሰማው የነበረው ስቃይ ለኃጢአተኛው ሰብዓዊ ዘር የሚደረገው የምህረት ምልጃ ካበቃ በኋላ ኃጢአተኞች ከሚሰማቸው ስቃይ ጋር ይመሳሰላል። የእግዚአብሔርን ልጅ የንዳውና የጠጣውንም ፅዋ እጅግ የመረረ ያደረገው በሰው ምትክ ሆኖ የእግዚአብሔርን ቁጣ እንዲቀበል ያደረገው የኃጢአት ምንነት ስለተሰማው ነው።

ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት

የአዳኛችንን ተስፋ የመቁረጥ ስቃይ መላእክት በመገረም ተመለከቱ። የሰማይ ሠራዊት ያን አስከፊ ትዕይንት ላለማየት ፊታቸውን ሸፈኑ። ግዑዙ ፍጥረትም ለተዋረደውና በሞት አፋፍ ላይ ላለው ፈጣሪዋ ማዘንዋን ገለፀች። በእኩለ ቀን ላይ ለመሬት ሙሉና ብሩህ ብርሃንዋን ትሰጥ የነበረችው ፀሀይ በድንገት ድርግም አለች።

አስከሬን የያዘ ሳጥን በጥቁር ግምጃ እንደሚሸፈን ዓይነት ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ መስቀሉን ሸፈነው። “ከቀኑም ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።” ይህ ጨረቃ ወይም ከዋክብት እንደሌሉበት እኩለ ሌሊት ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ የተከሰተው በፀሀይ ግርዶሽ ወይም በሌላ ተፈጥሮአዊ ክስተት ምክንያት አይደለም። ይህ ጨለማ ከዚያ ጊዜ በኋላ የሚመጣው ትውልድ እምነቱ የፀና እንዲሆን እግዚአብሔር ያዘዘው ተዓምራዊ ምስክርነት ነው።

ያ ጥቅጥቅ ጨለማ እግዚአብሔርን ከመታየት ከለለው። አብ ጨለማን ሸፋን አድርጎ ክብሩን ከሰብዓዊ ዓይን ሰወረ። በዚህ ወቅት እግዚአብሔርና መላእክቱ በመስቀሉ አጠገብ ነበሩ። እግዚአብሔር አብ ከልጁ ጋር ሆነ። ይሁን እንጂ ከዚያ መኖሩ አልተገለፀም። ክብሩ ዳመናውን አልፎ ቢገለጥ ኖሮ ከዚያ የነበሩት ሰዎች በሙሉ ያልቁ ነበር። ያ ቢሆን ደግሞ በእግዚአብሔር ከዚያ መገኘት ክርስቶስ አይፅናናም ነበር። የሱስ የወይን ጠጅ መጭመቂያውን ብቻውን ረገጠ ከህዝቡም አንድ ሰው ከእርሱ ጋር አልተገኘም።

እግዚአብሔር በልጁ ላይ የደረሰውን የመጨረሻ ሰብዓዊ ስቃይ በጥቅጥቅ ጨለማ ከለለው። ክርስቶስ ሲሰቃይ ያዩ ሁሉ መለኮታዊነቱን አውቀዋል። ያ ሰብዓዊ ፍጡራን ያዩት ፊት ፈፅሞ የሚረሳ አልነበረም። የቃየል ፊት ነፍሰ ገዳይነቱን እንዳሳወቀበት ሁሉ እንዲሁም በክርስቶስ ፊት ላይ የእግዚአብሔር ገፀ ባህርይ የሆነው ንፅህና፣ ፍፁም ሰላማዊነትና ርህሩህነት ይታይበት ነበር። የየሱስ ከሳሾች ግን ለሰማይ ማህተም ደንታ አልነበራቸውም። የሱስ የሚያፈዙበት ሰዎች ቀና ብለው እየተመለከቱት ለረጅም ሰዓታት ሲሰቃይ ቆየ፣ በኋላ ግን እግዚአብሔር በምህረቱ በካባው ከለለው።

በቀራንዮ ላይ የመቃበር ፀጥታ የሰፈነበት መሰለ። በመስቀሉ ዙርያ ተሰብስቦ የነበረው ሕዝብ ምክንያቱ ያልታወቀ ፍርሀት አስጨነቀው። ስድቡና እርግማኑ ሁሉ በድንገት ተቋረጠ። ወንዶች፣ ሴቶችና ልጆች በመሬት ላይ ተዘረሩ። አንዳንድ ጊዜ ዳመናውን ዘልቆ በሚታየው ብልጭታ አማካይነት መስቀሉና የተሰቀለው አዳኝ ይታዩ ነበር። ካህናቱ፣ ሹማምንቱ ፀሀፍት፣ ወንጀለኛ ስቃዮችና ለአድማ የተጠራው ሕዝብ ቅጣታቸውን የሚያገኙበት ጊዜ የመጣ መሰላቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንዳንድ ሰዎች የሱስ ከመስቀል ወርዶ ሊመጣ ነው እያሉ ማሾክሾክ ጀመሩ። አንዳንዶቹ ከፍርሀት የተነሳ እየጮኹና ደረታቸውን እየመቱ በዳበሳ ወደ ከተማው ለመመለስ ሞከሩ።

“ኤሎሄ! ኤሎሄ!”

በዘጠነኛው ሰዓት ህዝቡን የሸፈነው ጨለማ ቢወገድም የሱስን እንደ ከለለው ቆየ። ይህ ጨለማ የየሱስን ልብ ያስጨነቀው ስቃይ ምሳሌ ነበር። ማንም ሰብዓዊ ዓይን በመስቀሉ ዙሪያ የነበረውን ጨለማ አልፎ ለማየት እንዳልቻለ ሁሉ እንደዚሁም የክርስቶስን ነፍስ ከብቦ ያስጨንቃት የነበረውን ጥቅጥቅ ጨለማ አልፎ ለማየት የቻለ ማንም የለም። የሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ የመብረቅ ብልጭታው ወደ እርሱ የሚምዘገዘግ ይመስል ነበር። በዚህ ጊዜ የሱስ “ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማ ሰበቅታኒ?” “አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ” ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ። የሱስን ከብቦት የነበረው የውጨኛው የጨለማ ሽፋን በተነሳ ጊዜ ይህን ሰው ሰማይ ተበቅለው፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላለ የእግዚአብሔር ቁጣ ወረደበት የሚል የብዙ ሰዎች ጩኸት ተሰማ። በእርሱ ከሚያምኑ ሰዎች መካከል ብዙዎቹ ያሰማውን ጩኸት በሰሙ ጊዜ ተስፋ ቆረጡ። እግዚአብሔር የሱስን ከተወው ተከታዮቹ በምን መተማመን ይችላሉ?



ጨለማው ከተጨነቀው የክርስቶስ መንፈስ ላይ በተነሳ ጊዜ የሱስ የስጋዊ ስቃይ ተሰማውና “ጠማኝ” አለ። ከሮማውያን ወታደሮች አንዱ የደረቁት የየሱስን ከንፈሮች ስላየ አዝሞ “ስፖንጅ አምጥቶ ሆምጣጤ ሞላበት። በመቃ ላይ አድርጎም ሊየሱስ እንዲጠጣ አቀረበለት።” ካህናቱ ግን በየሱስ ስቃይ አፌዙ። መሬትዋ በጨለማ በተሸፈነች ጊዜ እነዚህ ካህናት በፍርሀት ተውጠው ነበር ነገር ግን ድንጋጤአቸው ከለቀቃቸው በኋላ የሱስ

ያመልጥ ይሆናል የሚል ስጋታቸው እንደገና አስጨነቃቸው። “ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማ ሰበቅታኒ?” ሲል የተናገረውንም አጣምመው ተረጎሙት። በከፍተኛ ንቀትና በማንቋሸሽ “ይህስ ኤልያስን ይጠራል!” ተባባሉ። “ቆይ እስቲ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደሆነ እንይ!” እያሉ ከስቃዩ ለማዳን የነበራቸውን የመጨረሻ ዕድል ነፈጉት።

እንከን የማይወጣለት የእግዚአብሔር ልጅ ሰውነቱ ቆሳስሎ፣ ለእርዳታ የሚዘረጉ እጆቹ በምስማር ከእንጨት ላይ ተቸንክረው፣ የፍቅር አገልግሎት ለመስጠት መጓዝ የማይሰለቻቸው እግሮቹ በግንድ ላይ በካስማ ተመትተው፣ ያ ንጉሣዊ ራሱ በሾህ አክሊል ተበሳስቶና የሚንቀጠቀጡት ከንፈሮቹ የወዮታ ጩኸት እያሰሙ በመስቀል ላይ ተንጠለጠለ። ከራሱ፣ ከእጆቹና፣ ከእግሮቹ የፈሰሰው ደም፣ መላ አካሉን ያጎሳቆለው ጣዕረ ሞት አባቱ ፊቱን ከእርሱ ስለመለሰ የተሰማው በአንደበት ሊገለፅ የማይቻል ስቃይ ሁሉ ተዳምሮ የእግዚአብሔር ልጅ ይህን ሁሉ የኃጢአት ፍዳ የተቀበለው የሞትን ኃይል አሸንፎ ለአንተ የነትን በር ለመክፈት ሲል ነው እያለ ለእያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡር የሚናገር መልእክት ነው። ኃይለኛውን የባህር ማዕበል ፀጥ ረጭ እንዲል አድርጎ በአረፋ የተሸፈነውን የውሀ ፈረሰኛ ያስወገደው፣ የጠፉ ዓይኖችን እንዲያዩ ያደረገውና ሙታንን ያስነሳው ጌታ አንተን ስለወደደህ ራሱን በመስቀል ላይ ሰዋ። የኃጢአት ተሸካሚ የሆነው ጌታ ፍትሀዊ የሆነውን መለኮታዊ ቁጣ ችሎ ለአንተ ሲል እንደ ኃጢአተኛ ሆነ።

“ተፈፀመ!”

ከዚያ ቆመው ይመለከቱ የነበሩት ሰዎች ፀጥ ብለው የአስፈሪውን ትዕይንት ፍፃሜ ይጠባበቁ ነበር። የፀሀይ ብርሃን ቢታይም መስቀሉ በጨለማ እንደተሸፈነ ቆየ። ካህናቱና ሹማምንቱ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለከቱ ከተማዋና የይሁዳ መስኮች በከባድ ዳመና ተሸፍነው አዩ። የፅድቅ ፀሀይና የዓለም ብርሀን የሆነው ጌታ በአንድ ወቅት ተወዳጅ ከነበረችው ከተማ ብርሃኑን አነሳ። አስፈሪ የሆነው የእግዚአብሔር የቁጣው ብልጭታ ለመጥፋት በተዘጋጀችው ከተማ ላይ ተነጣጠረ።

መስቀሉን ሸፍኖት የነበረው ጨለማ በድንገት እንደለቀቀ እንደ መለከት ከሩቅ በሚሰማ ድምፅ የሱስ “ተፈፀመ!” “አባት ሆይ! እነሆ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ!” ሲል ጮኸ። በዚያች ወቅት በመስቀሉ ላይ ብርሀን ስለወጣ



የአዳኛችን ፊት እንደ ፀሀይ በደመቀ ክብር አበራ። ከዚያ በኋላ ራሱን በደረቱ ላይ ጣል አድርጎ አረፈ።

በእግዚአብሔር ፈቃሞ ችላ የተባለ በመሰለበት በዚያ አስከፊ የጨለማ ወቅት ክርስቶስ የመጨረሻውን ሰብዓዊ የወዮታ ፅዋ ጠጣ። በዚያ እጅግ አስጨናቂ ጊዜ የሱስ የተማመነው ከዚያ በፊት በአባቱ ዘንድ ተቀባይነት እንደነበረው ባየው ማረጋገጫ ነው። የአባቱን ባህርይ፣ ፍርዱ ፍትሀዊ መሆኑን፣ መሀሪነቱንና ታላቅ ፍቅሩን ያውቅ ነበር። የሱስ የአባቱን ትእዛዝ ለመፈፀም ምንጊዜም ደስታኛ ስለነበር እምነቱን በዚህ አባቱ ላይ አደረገ። ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ስላስገዛ አባቱ እንደተለየው ይሰማው የነበረው ስጋት ለቀቀው፤ ስለዚህ ክርስቶስ በህይማኖት አሸናፊ ሆነ።

እንደዚህ ያለ ትእይንት በዓለም ከቶ ታይቶ አይታወቅም። በዚያ የነበሩት ሰዎች አፍዝ አደንግዝ እንደያዛቸው ሁሉ አፋቸውን ከፍተው አዳኛቸንን አንጋጠው ይመለከቱት ነበር። መሬት እንደገና በጨለማ ተሸፈነች፣ የነንድጓድ ድምፅም ተሰማ። ወዲያውኑ ከባድ የመሬት መናወጥ ደረሰ። በነውጡ ምክንያት ሰዎች እየተናጡ ተደራርበው ወደቁ። በአካባቢው ከነበሩ ጋራዎች የተሰነጠቀው አለት እንደ ናዳ እየተንከባለለ ወደ ደልዳላው ቦታ ወረደ። መቃብሮች ተከፍተው ሬሳዎች እየተስፈነጠሩ ወጡ። መላው ፍጥረት የሚንቀጠቀጥ መሰለ።

ካህናት፣ ሹማምንት፣ ወታደሮች፣ ወንጀለኛ ሰቃዮች ከዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉ እንደ ድዳ አንደበታቸው ታስሮ በመሬት ላይ ተዘረሩ።

“ተፈፀመ!” የሚለው ጩኸት ከየሱስ አንደበት በወጣበት ወቅት ካህናት በቤተ መቅደሱ ውስጥ ስርዓተ አገልግሎት ያካሂዱ ነበር። ጊዜው የምሽት መስዋዕት የሚቀርብበት ሰዓት ስለነበር የየሱስ ምሳሌ የሆነው የመስዋዕት በግ ለመታረድ ቀረበ። ካህኑ የተዋበውን ልብሰ ተክህኖ ተጎናፅፎ አብርሀም ልጁን ለመሰዋት በተዘጋጀ ጊዜ እንዳደረገው ቢላዋውን በእጁ ይዞ ቆመ። ህዝቡም በከፍተኛ ጉጉት ይመለከቱ ነበር። ነገር ግን ጌታ ራሱ ስለቀረበ መሬት ተናወጠች። የቤተ መቅደሱን የውስጠኛውን መጋረጃ የማይታይ እጅ ከላይ እስከ ታች ተርትሮ ከሁለት ስለከፈለው በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር ክብር መግለጫ የነበረው ቦታ ለህዝቡ ክፍት ሆኖ ታየ። የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥ የነበረው የፅላቱ ክዳን በሆነው የስርየት መክደኛ ከሚባለው በላይ ነበር። ይህን ክፍል ከሌሎቹ የቤተ መቅደሱ ክፍሎች የሚለየውን መጋረጃ መክፈት የሚፈቀድለት ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበር። ሊቀ ካህኑ በዓመት አንድ ጊዜ የህዝቡን ኃጢአት ለማስተሰረይ ወደዚህ ክፍል ይገባ ነበር።



አሁን ግን ይህን ክፍል (ቅድስተ ቅዱሳን) ከሌላው የሚለየው መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተቀደደ። ስለዚህ የምድራዊ ቤተ መቅደስ ቅድስተ ቅዱሳን ቅድስናው አከተመ።

የቤተ መቅደሱ መጋረጃ መቀደድ ትልቅ ፍርሀትና ትርምስ አስከተለ። ካህኑ ለመስዋዕት የቀረበውን በግ ለማረድ ተዘጋጅቶ ነበር። ነገር ግን ቢላዋው ከእጁ ወደቀ በጉም አመለጠ። በእግዚአብሔር ልጅ ሞት ምሳሌያዊው መስዋዕት በእውነተኛው መስዋዕት ተተካ። ትልቁ መስዋዕት ተሰዋ። **ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግቢያው በር ተከፈተ። ለሁሉም አዲስና ህያው መንገድ ተዘጋጀ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ኃጢአተኛና ያዘኑ ሰብዓዊ ፍጡራን የሊቀ ካህን መምጣት መጠበቅ አላስፈለጋቸውም።** ከዚያ ጊዜ በኋላ አዳኛችን ካህንና ጠበቃ ሆኖ በሰማየ ሰማያት ያገለግላል። የቤተ መቅደሱ መጋረጃ በተቀደደ ጊዜ አንድ ድምፅ ለስግደት ለመጡት ሰዎች ለኃጢአት ስርየት የሚቀርበው መስዋዕትና ቁርባን አከተመ ያላቸው ይመስል ነበር። የሱስ በቃሉ መሰረት “እምላኬ ሆይ! በመፅሀፍ ስለ እኔ እንደተፃፈ ፈቃድህን ለመፈፀም መጥቻለሁ፣” አለ፤ “በዚህ ሁኔታ ሁለተኛውን ዓይነት መስዋዕት በቦታው ለመተካት የመጀመሪያውን ዓይነት መስዋዕት ሽሮአል”፤ “ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ በማያዳግም ሁኔታ መስዋዕት ሆኖ በመቅረቡ ምክንያት ተቀድሰናል”፤ “ክርስቶስ ግን ለዘላለም የሆነውን አንዱን መስዋዕት ካቀረበ በኋላ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦአል” ዕብ. 10:7፣ 9፣ 10፣ 12። ገዘ

(ይህ ጽሁፍ “ቀራንዮ” በሚል ርዕስ “የዘመናት ምኞት” በተባለው መጽሐፍ ምዕራፍ 78 ላይ ይገኛል፤ ጽሁፉ የተመሠረተው ማቴ. 27:31-53፣ ማር. 15:20-38፣ ሉቃ. 23:26-46፣ ዮሐ. 19:16-30 ላይ ነው፤ ተርጓሚ አበበ ብዙነህ)


“ክርስቶስ ግን ለዘላለም የሆነውን አንዱን መስዋዕት ካቀረበ በኋላ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦአል” ዕብ. 10:12

“ጌታ ተነስቷል!”

ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ ያለው ሌሊት ቀስ በቀስ ሊነጋ ተቃረበ። ነህ ከመቅደዱ በፊት ያለው ከባድ የጨለማ ሰዓት ደረሰ። እስከዚያ ሰዓት ድረስ ክርስቶስ በጠባብዋ መቃብር ውስጥ እንደ እስረኛ ሆኖ ቆየ። በዚያ ሰዓት የመቃብሩ በር የተዘጋበት ትልቅ ድንጋይና ማሸጊያው ማኅተም እንዳለ ሲሆን የሮማውያን ወታደሮችም በዙሪ ጥበቃ ሥራቸው ላይ ነበሩ። እንደዚሁም በዓይን የማይታዩ የርኩስ መንፈስ ሠራዊት የመቃብሩን ቦታ ከብበው ይጠብቁ ነበር። የሚቻለው ቢሆን ኖሮ ሰይጣን የክህደት ሥራዊቱን በማስተባበር የእግዚአብሔርን ልጅ በመቃብር ውስጥ ለማስቀረት መቃብሩን ለዘላለም ታሽጎ እንዲኖር ለማድረግ ይፈልግ ነበር። ነገር ግን ከሰይጣን ሠራዊት የበለጠ ኃይል ያላቸው የሰማይ መላእክት የህይወት ጌታን ለመቀበል በመቃብሩ ዙሪያ ተሰበሰቡ።

“እነሆ ታላቅ መናወጥም ሆነ። የእግዚአብሔር መልክተኛ ከሰማይ ወርዷልና።” ይህ መልአክ የእግዚአብሔርን ግርማ ሞገስ ተጎናፅፎ ከሰማይ በወጣ ጊዜ የእግዚአብሔር የክብሩ ብርሃን ከፊት ለፊቱ እያበራ ይመራው ነበር። “የመልአኩ ፊት እንደ መብረቅ ያበራ ነበር፣ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ጠባቂዎቹ መልአኩን ከመፍራት የተነሳ በመንቀጥቀጥ እንደ በድን ሆኑ።”

ካህናትና ሹማምንት ሆይ! የዘበኞቻችሁ ኃይል የት ደረሰ? የሰውን ኃይል ፈርተው የማያውቁት ጀግና ወታደሮች ጦርና ጎራዴ በሌለበት ጦርነት እንደተማረኩ ሆኑ። እነዚያ መቃብሩን ለመጠበቅ የተመደቡ ወታደሮች ያዩት ሟች የሆነ የሰብአዊ ጦረኛ ፊት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ሠራዊት መካከል እጅግ በጣም ኃያል የሆነውን መልአክ ፊት ነው። ይህ የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሰይጣንን (ሰይጣን ከሰማይ ከመውደቁ በፊት የነበረውን) ማዕረግ የወረሰ ነው። በቤተልሔም ኮረብታዎች ላይ የክርስቶን ልደት ያበሰረውም እርሱ ነው። ይህ መልእክተኛ በቀረባት ጊዜ መሬት ተናወጠች፣ የሰይጣን ሰራዊትም ሸሹ። በመቃብሩ በር ላይ የነበረውን ድንጋይ ባንከባለለው ጊዜ መላው ሰማይ ወደ ምድር የወረደ ይመስል ነበር። ወታደሮቹ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ያን ትልቅ ድንጋይ እንደ ጠጠር ሲወረውረው ተመለከቱ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ! አባትህ ይጠራሀል ውጣ እያለ ሲጮኽ አዳመጡ። ወዲያውኑ የሱስ ከመቃብር ሲወጣ ከማየታቸውም ሌላ በተከፈተው መቃብር ላይ ሆኖ “እኔ ነኝ ትንሳኤ ህይወትም፣” ብሎ ሲናገር ሰሙት። የሱስ ግርማ ሞገስ ተጎናፅፎ ከመቃብር በወጣ ጊዜ የመልአክ ሠራዊት በአክብሮት እየሰገዱና የውዳሴ መዝሙር እየዘመሩ ተቀበሉት።


© General Conference of Seventh-day Adventists. All rights reserved. Do not use without permission.


የሱስ ህይወቱን አሳልፎ በሰጠበት ሰዓት መሬት ተንቀጥቅጣ ነበር፣ እንደዚሁም ህይወቱን በድል አድራጊነት ባስመለሰበት ሰዓት መሬት ተንቀጠቀጠች። ሞትንና መቃብርን ያሸነፈው ጌታ በድል አድራጊነት ከመቃብር በወጣ ጊዜ መሬት ተንቀጠቀጠች፣ የመብረቅ ብልጭታ ታየ፣ የነጎድጓድ ድምፅም ተሰማ። ጌታ የሱስ ወደዚች ዓለም ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ምድር ብቻ ሳትሆን ሰማይ ጭምርም ይናወጣል፤ “ምድር ራስዋ እንደ ሰከረ ሰው ትንገዳገዳለች፣ በአውሎ ነፋስ እንደተገፋ ጎጆም ትናወጣለች”፤ “ሰማይም እንደ ብራና ተጠቅልሎ ይወገዳል”፤ “ፍጥረት ሁሉ በእሳት ተቃጥሎ ይጠፋል። ምድርና በእርስዋ ላይ ያለው ነገር ሁሉ ይቃጠላል”፤ ”እግዚአብሔር ግን የሕዝቡ መጠጊያ (ተስፋ) ነው። ለእስራኤልም ልጆች ኃይል ነው” (ዕብ. 12፡26፤ ኢሳ. 24፡20፤ 34፡4፤ 2ጴጥ. 3፡10፤ ኢዮኤል 3፡16)።

የሱስ በሞተ ጊዜ ወታደሮቹ መሬቷ በእኩለ ቀን በጨለማ ስትሸፈንና እንደዚሁም በትንሳኤው ጊዜ መላእክት ሌሊቱ እንደ ቀን እንዲያበራ ሲያደርጉ አይተዋል፤ በተጨማሪም የሰማይ ነዋሪዎች አንተ የሰይጣንንና የጨለማን ኃይል ያሸነፍህ፣ ሞትንም ድል ያደረግህ ነህ እያሉ ለክርስቶስ በታላቅ ደስታ በድል አድራጊነት ስሜት ሲዘምሩለት ሰምተዋል። ሮማውያን ወታደሮች ክርስቶስ በክብር ከመቃብር ሲወጣ አይተዋል። ከጥቂት ጊዜ በፊት ባፌዙበትና በተሳለቁበት ጌታ ፊት ላይ ዓይኖቻቸውን ተክለው ተመለከቱ። ይህን ባለግርማ ሞገስ ፊት ባዩ ጊዜ በፍርድ ቤቱ አዳራሽ ያዩትና የሾህ አክሊል የደፉበት እስረኛ ትዝ አላቸው። በደረሰበት የጭካኔ ግርፋት

ምክንያት ሰውነቱ ተላልጦ ያለ አንዳች ማጉረምረም በሄሮድስና በጲላጦስ ፊት ቆሞ የነበረው እርሱ መሆኑን አስታወሱ። በመስቀል ላይ በምስማር ተቸንክሮ ሳለ ካህናቱና ሹማምንቱ ከመጠን በላይ በመደሰት "ሌሎችን አዳነ ራሱን ግን ማዳን አይችልም፣" (ማቴ. 27፡42) እያሉ ራሳቸውን የነቀነቁበት እርሱ መሆኑን አወቁ። በአዲሱ የዮሴፍ መቃብር ውስጥ የነበረውም እርሱ ራሱ ነው። በመለኮት አዋጅ ከመቃብር ግዞት ነፃ ስለወጣ በመቃብሩ ላይ የነበረው ግዙፍ ተራራ ሊያስቀረው አልቻለም።

ሮማውያኑ ወታደሮች መላእክቱንና ባለ ግርማ ሞገሱን አዳኝ ባዩ ጊዜ ህሊናቸውን ስተው በመውደቅ እንደ በድን ሆኑ። ይህ ሰማያዊ ሠራዊት ከዓይናቸው እንደተሰወረ ከወደቁበት ቦታ ተነስተው እየተርበተበቱ በሩጫ ወደ አትክልቱ በር ሄዱ። እንደ ሰከረ ሰው እየተንገዳገዱ ወደ ከተማው ሄደው ላገኙት ሁሉ የደረሰባቸውን አስገራሚ ነገር ተናገሩ። እነርሱ ቀጥታ ወደ ጲላጦስ ለመሄድ አስበው ነበር፣ ነገር ግን የአይሁድ መሪዎች ወሬውን ሰምተው ስለነበር ወታደሮቹ መጀመሪያ ወደ እነርሱ እንዲመጡ ላኩባቸው። ወታደሮቹ ፊታቸው ገርጥቶ በፍርሀት ይንቀጠቀጡ ስለነበር ክርስቶስ ከሞት የመነሳቱ ታሪክ በፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር። ወታደሮቹ ሌላ ነገር ለማሰብ ወይም ለማውራት ጊዜ ስላልነበራቸው ያዩትን ሁሉ አንድም ሳያስቀሩ ተናገሩ። ጭንቀት በተሞላበት አነጋገር የተሰቀለው የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ መልአኩ የሰማይ ባለግርማ፣ የክብር ንጉሥ እያለ ሲጠራው ሰምተናል አሉ።

የካህናቱ ፊት እንደ ሬሳ ፊት ሆነ። ቀያፋ ለመናገር ቢሞክርም ከንፈሩ ተንቀሳቀሰ እንጂ የተሰማ ድምፅ አልነበረም። ወታደሮቹ ታሪኩን ተናግረው እንዳበቁ ከሸንጎው አዳራሽ ሊወጡ ሲሉ አንድ ድምፅ እንዲቆዩ



ነገራቸው። ቀያፋ እንደ ምንም ብሎ ለመናገር ስለቻለ ቆዩ፣ ያያቸሁትን ለማንም አትናገሩ አላቸው።

ወታደሮቹ "እኛ ተኝተን ሳለ ደቀ መዘሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት፣" የሚል የሀሰት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ነገራቸው። ይህን በማድረጋቸው ካህናቱና ሹማምንቱ ራሳቸውን ትዝብት ላይ ጣሉ። ወታደሮቹ እንዴት ደቀ መዘሙርቱ ተኝተን ሳል አስከሬኑን ሰረቁብን ማለት ይችላሉ? ተኝተው ከነበረስ መስረቁን እንዴት አወቁ? ደቀ መዘሙርቱ የየሱስን አስከሬን መስረቃቸው ከተረጋገጠ መጀመሪያ የሚወነጅሉዋቸው ካህናቱ አልነበሩምን? መቃብሩን ይጠብቁ የነበሩት ዘበኞች ተኝተው ከሆነስ እነርሱን በጲላጦስ ፊት ለመክሰስ የመጀመሪያ የሚሆኑት ካህናቱ አይደሉምን?

ወታደሮቹ በሥራ ላይ እያሉ እንደተኙ ለማስመሰል የቀረበው አሳብ እጅግ አስደነጣቸው። በዚያን ጊዜ በሥራ ላይ እያሉ ተኝተው መገኘት በሞት የሚያስቀጣ ጥፋት ነበር። ታዲያ ሀሰት በመናገር ህዝቡን አታልለው የራሳቸውን ህልውና ለአደጋ ያጋልጡን? የጥበቃ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት እንቅልፍ በዓይናቸው ሳይዞር በትጋት ሲጠብቁ አላደሩምን? ለገንዘብ ሲሉ ራሳቸውን ቢያታልሉ እንኳ ምርመራውን እንዴት ሊቋቋሙ ይችላሉ?


ካህናቱ ሥጋት ያሳደረባቸው ምስክርነት እንዳይሰፋፋ ለማድረግ ሲሉ ጲላጦስም እንደ እነርሱ ወሬው እንዲስፋፋ የማይፈልግ መሆኑን ለወታደሮቹ አስረድተው ለህይወታቸው ደህንነት ኃላፊነቱን እንደሚወስዱ ቃል ገቡላቸው። በዚህ መሠረት ወታደሮቹ ታማኝነታቸውን በገንዘብ ሸጡ። እነዚህ ወታደሮች አስደናቂ የሆነ የእውነት መልእክት ይዘው ወደ ካህናቱ መጡ፤ ነገር ግን ገንዘብና በሉ የተባሉትን የሀሰት ሪፖርት ይዘው ተመለሱ።

ይህ በዚህ እንዳለ ጲላጦስ የየሱስን ከሞት መነሳት አስቀድሞ ሰማ። ምንም እንኳን የሱስን እንዲሞት አሳልፎ መስጠቱ በኃላፊነት የሚያስጠይቀው ቢሆንም ጲላጦስ ብዙ ጭንቀት አልተሰማውም። በየሱስ ላይ የፈረደበት ያለፍላጎቱና የርህራሄ መንፈስ እየተሰማው ቢሆንም የየሱስን መነሳት እከሰማበት ጊዜ ድረስ ልባዊ ፀፀት አልተሰማውም ነበር። አሁን ግን ከፍተኛ ፍርሀት ስለተሰማው ከማንም ጋር ላለመገናኘት ሲል ቤቱን ዘግቶ ተቀመጠ። ነገር ግን ካህናቱ ወደ እርሱ ሄደው ራሳቸው የፈጠሩትን የውሸት ታሪክ ከነገሩት በኋላ ወታደሮቹ በጥበቃ ሥራ ላይ ሳሉ ላደረሱት ጥፋት ይቅርታ እንዲያደርግላቸው ለመኑት። ይህን ለማድረግ ከመስማማቱ በፊት ጲላጦስ ዘበኞቹን ጠርቶ በግል አነጋገራቸው። እነርሱም ለደህንነታቸው በመሥጋት አንድም ነገር

ሳይደብቁ ስለነገሩት ጲላጦስ ስለደረሰው ነገር ትክክለኛ ግንዛቤ አገኘ። ስለ ጉዳዩ ብዙ ክትትል ባያደርግም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሰላም አልነበረውም።

የሱስ በመቃብር ውስጥ በነበረ ጊዜ ድሉ የሰይጣን ሆነ። ሰይጣን የሱስ እንደገና ህያው አይሆንም የሚል አጉል ተስፋ ነበረው። የክርስቶስ አስከሬን ለእኔ ይገባኛል በማለትና ክርስቶስን እስረኛ አድርጎ ለማስቀረት በመመኘት መቃብሩን በራሱ ዘበኞች አስጠበቀ። ሰማያዊዩ መልእክተኛ በመጣ ጊዜ የእርሱ መላዕክት ሲሸሹ ባየ ጊዜ እጅግ ተናደደ። ክርስቶስ በድል አድራጊነት ከመቃብር ሲወጣ ባየው ጊዜ የእርሱ መንግሥት አንድ ቀን እንደሚፈፀምና እርሱም የኋላ ኋላ እንደሚሞት አወቀ።

ክርስቶስ እንዲሞት በማድረጋቸው የእስራኤል ካህናት የሰይጣን መሣሪያ ስለሆኑ ሙሉ በሙሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ዋሉ። ሊወጡ ከማይችሉት ወጥመድ ውስጥ ስለገቡ በየሱስ ላይ በከፈቱት ጦርነት ከመግፋት በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። የየሱስን ከሞት መነሳት በሰሙ ጊዜ ህይወታቸው በአደጋ ላይ እንደሚወድቅ በማወቅ ህዝቡን ፈሩት። ስለዚህ የነበራቸው ብቸኛ ተስፋ የክርስቶስን ትንሳኤ በመካድ የእርሱን አታላይነት ማሳመን ነው። በዚህ መሠረት ወታደሮቹን በገንዘብ ሸነገሉ፣ ጲላጦስንም ዝም አሰኙ። የሀሰት ወሬአቸውን በሰፊው አሰራጩ፣ ይሁን እንጂ ዝም ሊያሰኙዋቸው የማይችሉ ምስክሮች አጋጠሙዋቸው። ብዙ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ከሞት መነሳት ወታደሮቹ የሰጡትን ምስክርነት ሰምተው ነበር። ከክርስቶስ ጋር ከሞት የተነሱ ሰዎችም ምስክርነታቸውንም የሰሙ ግለሰቦች ያዩትንና ሰሙትን ለካህናቱ ነገሯቸው። ካህናቱና ሹማምንቱ የሱስ በመንገድ ላይ ወይም በየመኖሪያ ቤታቸን ፊት ለፊት ይመጣብን ይሆን የሚል ሥጋት አስጨነቃቸው። የበር ቁልፍ ወይም መቀርቀሪያ ከእግዚአብሔር ልጅ ሊጠብቃቸው አልቻለም። በፍርድ ቤቱ አዳራሽ ውስጥ “ደሙ በኛ በልጆቻችንም ላይ ይሁን” (ማቴ. 27፡25) ብለው በጮኹ ጊዜ የነበረው አስፈሪ ትዕይንት ቀንም ሌሊትም በፊታቸው ላይ ተደቅኖ ይታያቸው ነበር። ያ ትዕይንት ከኅሊናቸው ሊጠፋ አልቻለም። የሰላም እንቅልፍ ማግኘትም አልቻሉም።



ኃያሉ መልአክ በክርስቶስ መቃብር አጠገብ ሆኖ አባትህ ይጠራሀል የሚል ጥሪ ባሰማ ጊዜ አዳኛችን በህያውነት ባህርዩ ከመቃብር ወጣ። በዚያን ጊዜ “እንደገና መልሼ የምወስዳት ህይወቴን አሳልፌ ለመስጠት ፈቃደኛ ስለሆንሁ አብ እኔን ይወድደኛል። ህይወቴን በፈቃዴ አሳልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ የሚወስዳት ማንም የለም። ህይወቴን አሳልፌ ለመስጠትና መልሼም ለመውሰድ መብት (ኃይል) አለኝ”፤ “ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱትና እኔ በሶስት ቀን እሠራዋለሁ” ብሎ የተናገረው ቃል እውነተኛነት ተረጋገጠ” (ዮሐ. 10፡17፤ 18፤ 2፡19)።

በተከፈተው በዮሴፍ መቃብር ላይ ሆኖ የሱስ በድል አድራጊነት “እኔ ነኝ ትንሳኤ ህይወትም” ሲል አውጇል። እነዚህን ቃላት መናገር የሚችል መለኮታዊ ባህርይ ያለው ብቻ ነው። ማንኛውም ፍጡር የሚኖረው በእግዚአብሔር ፈቃድና ኃይል ነው። ማንኛውም ፍጡር አካል የእግዚአብሔር ህይወት ጥገኛ ነው። ከከፍተኛው ሱራፌል እስከ ኢምንቷ ህዋስ ድረስ ያሉት ፍጡር አካላት ሁሉ የህይወት ምንጭ ከሆነው አምላክ ለህይወት የሚያስፈልጋቸውን ነገር ያገኛሉ። ህይወቴን አሳልፎ ለመስጠትና መልሼ ለመውሰድ ኃይል አለኝ ማለት የሚችል ከእግዚአብሔር ጋር የባህርይ አንድነት ያለው ብቻ ነው። ክርስቶስ በመለኮታዊነቱ የሞትን ማሠሪያ የሚበጥስ ኃይል አለው።

ክርስቶስ በሞት ላንቀላፉት ሁሉ የመጀመሪያ ምሳሌ ሆኖ ተነሳ። በካህኑ እጅ ወደላይና ወደታች የሚወዘወዘው እህል ነዶ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር፤ በመሆኑም ነዶው በእግዚአብሔር ፊት በሚቀርብበት ቀን ክርስቶስ ከሞት ተነሳ። ይህ ምሳሌያዊ አገልግሎት ለአንድ ሺ ዓመታት ያህል ሲካሄድ ቆየ። ከየእርሻ ማሳው የሚሰበሰበውን የመጀመሪያ የእህል ነዶ ሕዝቡ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይዘው ይሄዱና በእግዚአብሔር ፊት የምስጋና መባለጫ መባ ሆኖ ሲቀርብ ካህኑ ወደላይና ወደታች ያወዛውዘዋል። በማሳው ላይ ያለው የእህል አዝመራ

የሚታጨደውና የሚከመረው የመጀመሪያው ነዶ ለእግዚአብሔር ከቀረበ በኋላ ነው። ለእግዚአብሔር የሚቀርበው የመጀመሪያው ነዶ የመላው አዝመራ ምሳሌ ነው። እንደዚሁም ለሚሰበሰበው ትልቅ መንፈሳዊ አዝመራ ምሳሌ ነው። የእርሱ ትንሳኤ የሞቱ ፃድቃን እንደሚነሱ ምሳሌና ማረጋገጫ ነው። "የሱስ ሞቶ እንደተነሳ ካመንን እንዲሁም በየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና" (1ተሰ. 4፡14)።

የሱስ ከመቃብር ሲነሳ ብዙ ምርኮኞችን ይዞ ወጣ። ክርስቶስ በሞተ ጊዜ የደረሰው የመሬት መናወጥ የብዙ ሙታንን መቃብር ስለከፈተ በእነዚህ መቃብሮች ውስጥ የነበሩ ሙታን እርሱ በተነሳ ጊዜ አብረው ተነሱ። ከክርስቶስ ጋር የተነሱት ሰዎች የእግዚአብሔር የስራ አጋሮች የነበሩና ስለ እውነት በመመስከር ህይወታቸውን ያሳለፉ ናቸው። አሁን ከሞት ላስነሳቸው ጌታ ምስክር ሆኑ።

ክርስቶስ በአገልግሎቱ ጊዜ ሙታንን አስነስቷል። በናይን ከተማ የምትኖረውን የመበለት ልጅ፣ የምኩራብ አለቃውን ሴት ልጅና አልዓዛርን ከሞት አስነስቷቸዋል። እነዚህ ሁሉ እንደገና ሟቾች ስለነበሩ ለዘላለም የመኖር ባህርይ አልተሰጣቸውም ነበር። ከክርስቶስ ጋር አብረው የተነሱት ግን ዘላለም ህያው ሆኖ ለመኖር ነው የተነሱት። በሞትና በመቃብር ላይ ለተቀዳጀው ድል እንደ ምርኮኛ ሆነው ወደ ሰማይ ተወሰዱ። እኔ አድኛቸዋለሁና ከእንግዲህ የሰይጣን ምርኮኞች አይደሉም፤ የስቃዩ የመጀመሪያው ፍሬዎች እንዲሆኑ ከመቃብር አውጥቼ ሁለተኛ ሞትና ሀዘን ሳያዩ ለዘላለም ከእኔ ጋር እንዲኖሩ አምጥቻቸዋለሁ አለ የሱስ።

እነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ለብዙ ሰዎች ታዩ፣ ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳና እነርሱንም እንዳስነሳቸው መሰከሩ። በእነርሱ ምስክርነት የትንሳኤ እውንነት ተረጋገጠ። እነዚህ ከሞት የተነሱ ቅዱሳን "ከወገኖቻችን መካከል የሞቱት ተነስተው በህይወት ይኖራሉ፣ በድናቸውም እንደገና ህይወት ያገኛል" የሚለው እውነት ለመሆኑ ማስረጃ ናቸው። የእነርሱ ትንሳኤ "ወደ መቃብር የወረዱ ሁሉ ተነስተው በደስታ እልል ይላሉ። የጠል ነጠብጣብ ለምድር ህይወትን እንደሚሰጥ እግዚአብሔርም ከሞቱ ብዙ ጊዜ የሆናቸው ተነስተው በህይወት እንዲኖሩ ያደርጋል" የሚለው ትንቢት እንደሚፈፀም ማስረጃ ነው (ኢሳ. 26፡19)።



ለምዕመናን ክርስቶስ ትንሳኤና ህይወት ነው። ክርስቶስ ህይወት ስለሆነና ህይወትን መስጥት ስለሚችል በኃጢአት የጠፋን ህይወት ይመልሳል። እርሱ ዘላለማዊነትን የመስጠት ሙሉ ሥልጣን አለው። በሰብዓዊነቱ አሳልፎ የሰጣትን ህይወቱን መልሶ በመውሰድ ለሰብዓዊ ፍጡራን ይሰጣታል። "እኔ ግን የመጣሁት ህይወት እንዲያገኙና የተትረፈረፈ ህይወት እንዲኖራቸው ነው።" "እኔ ከምሰጠው ውሀ የሚጠጣ ለዘላለም ከቶ አይጠማም ምክንያቱም እኔ የምሰጠው ውሀ ለሚጠጣው ሰው ለዘላለም ህይወት የሚፈልቅ ምንጭ ይሆናል።" "ሥጋዬን የሚበላና ደሜንም የሚጠጣ ሁሉ የዘላለም ህይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን ከሞት አስነሳዋለሁ"።(ዮሐ. 10፡10፤ 4፡14፤ 6፡54)።

ለሚያምን ሰው ሞት ከባድ ነገር አይደለም። ክርስቶስ ሞት የአጭር ጊዜ ጉዳይ መሆኑን ይናገራል። "ቃሌን የሚጠብቅ ከቶ አይሞትም"፤ "ሕይወታችሁ የሆነው ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ እናንተ ከእርሱ ጋር ትገለጣላችሁ፤ የክብሩም ተካፋዮች ትሆናላችሁ" (ዮሐ. 8፡51፤ ቆላ. 3፡4)።

በመስቀል ላይ "ተፈፀመ!" ተብሎ በጩኸት የተነገረውን ቃል ሙታን ሰምተውታል። ይህ ቃል የመቃብርን ግድግዳ አልፎ በመግባት ያንቀላፉ ሙታንን ቀሰቀሰ። የክርስቶስ ድምፅ ከሰማይ በሚሰማበት ጊዜ ይህ ሁኔታ በድጋሚ ይፈፀማል። የክርስቶስ ድምፅ በመቃብር ውስጥ ስለሚሰማ በክርስቶስ የሞቱ ሁሉ ይነሳሉ። ክርስቶስ ከሞት በተነሳ ጊዜ የተከፈቱ መቃብሮች ጥቂቶች ነበሩ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጣ ግን በእርሱ ዘንድ ተወዳጅ የሆኑ ሙታን ሁሉ ክቡርና ዘላለማዊ ህይወት ለመኖር ይነሳሉ። ክርስቶስን ከሞት እንዲነሳ ያደረገው ኃይል የእርሱን ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም ዓለም ከማንኛውም ሥልጣን፤ ኃይልና ስም ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያደርጋታል። ገዛዉ

(ምንጭ፤ "የዘመናት ምኞት"፤ ምዕራፍ 81፤ ጽሁፉ የተመሠረተው ማቴ. 28፡2-4፤ 11-15፤ ተርጓሚ **አበበ ብዙነህ**)

ሞኝነት ወይስ ...?

ፓ/ር ስምረት መሐሪ

“የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና” (1ቆሮ. 1፡18)

በዚህች በምንኖርባት ምድር በነጻ የምናገኘው ነገር የለም። ለምናገኛቸው ነገሮች ሁሉ በሆነ መንገድ ዋጋ እንከፍላለን። ባንከፍል እንኳን ሁልጊዜ ውለታ መላሾች መሆናችን ይሰማናል። ስለዚህም ይሆናል አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የሆነ መልካም ነገር ሲያደርጉልን ባለዕዳ የሆንን መስሎ የሚሰማን እና “ውለታ መላሽ ያድርገኝ” ወይም “አንተ እኮ ባለውለታዬ ነህ!” ብለን የምንናገረው።

መልካም አድራጊው ሰውም ምንም እንኳን በቀጥታ ባይናገርም፣ ለሌሎች ሰዎች የሠራቸውን ውለታዎች በማሰብ አብዛኛውን ጊዜ ውስጣዊ ኩራት ይሰማዋል። በሠራው ጥሩ ሥራ መጠን ምስጋና እና ምላሽ ሳያገኝ ሲቀር ደግሞ “እኔ ሁልጊዜ ሰውን እረዳለሁ፣ ምላሽ ግን አላገኝም” ወይም ደግሞ “እኔ ይሄንን ሁሉ ነገር ሳደርግለት፣ እርሱ ግን አንድም ነገር አድርጎልኝ አያውቅም” ብሎ ያስባል። ያለከፍያ መልካምን ማድረግ ጅልነት መስሎ ይታየዋል።



ከእነዚህ ምሳሌዎች ሁለት ነገሮችን እንረዳለን፡- 1ኛ) መልካም ነገር የሚደረግላቸው ሰዎች ድርጊቱን እንደስጦታ ሳይሆን፣ መመለስ እንዳለበት ውለታ ይመለከቱታል። 2ኛ) በአንዳሩም ደግሞ፣ መልካም አድራጊዎች ለበጎ ድርጊታቸው ምስጋና ወይም መልስ ሳያገኙ ከቀሩ እንደተጎዱ ይሰማቸዋል።

ሁለተኛውን ነጥብ በአንድ ገጠመኝ ጎላ ላድርገው፡- አሠራበት በነበረ አንድ ቦታ አብራኝ ትሠራ የነበረች የሥራ ባልደረባዬ፣ መሥሪያ ቤቱ አንድ ልምምድ እንደነበረው አጫወተችኝ። ይኸውም፣ የሠራተኞች ልደት በደረሰ ጊዜ ለባለልደቱ ገንዘብ አዋጥቶ የልደት ስጦታ የመግዛት ልምድ ነበር። ይሄ ልምምድ ግን አሁን እንዳቆመ ስትነግረኝ፣ “ያቆመበት ምክንያት ምንድን ነው?” ብዬ ጠየኳት። እርሷም፣ ሁልጊዜ የአንድ የሥራ ባልደረባ የልደት ቀን ሲደርስ ገንዘቡን አሰባስባ ስጦታውን የምትገዛ እርሷ እንደነበረች፣ የእርሷ ልደት ሲደርስ ግን የሥራ ባልደረቦቿዋ ለእርሷ ገንዘብ በማዋጣት ስጦታ ገዝተው እንዳላበረከቱላት ነገረችኝ። በዚህም ምክንያት “እኔን የማያስቡኝ ከሆነ፣ እኔ ለምን ለእነርሱ አስባለሁ?” በማለት መዋጮ በማሰባሰብ ለባለልደት የሥራ ጓደኞቿ ስጦታን መስጠት አቆመች።

ስለዚህ ሰዎች ስንባል በነጻ ሲሰጠን ውለታ መመለስ እንዳለብን፣ በነጻ ስንሰጥ ደግሞ ምላሽ ማግኘት እንዳለብን ይሰማናል። ከሕጻንነታችን ጀምሮ በእንደዚህ አይነት መልክ ነው ያደግነው። “ጥሩ ልጅ ከሆንህ፣ እወድሃለሁ፣ ... ስጦታ እሰጥሃለሁ፣ ... አስቸጋሪ ልጅ ከሆንህ ግን ጅቡ ይበላሃል፣ ... አላናግርህም፣ ... ልጄ አይደለህም ...” እንላለን፤ ወይም ስንባል አድግናል። ከዚህም የተነሳ የምንሰጠው ወይም የምንቀበለው ፍቅር ሁልጊዜ በድርጊት ላይ የተመሠረተ ነው። ያለተጨባጭ ምክንያት መውደድን ወይም መወደድን አናውቅም። ስለዚህም ይመስለኛል “የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው” የተባለው።

ለመሆኑ የመስቀሉ ቃል ምንድን ነው? የመስቀሉ ቃል ወንጌል ነው! ወንጌልስ ምንድን ነው? ወንጌል መልካም ዜና ነው! መልካሙስ ዜና ምን ይላል? “የምድር ሰዎች ሁሉ ስሙኝ! እኔ ፈጣሪያችሁ ነኝ፣ በጣም እወዳችኋለሁ! በግድየለሽ አኗኗራችሁ እኔ ለእናንተ ስላለኝ ስሜት ግድ እንደማይሰጣችሁ ብታሳዩኝም፣ እኔ ግን እወዳችኋለሁ! ስለዚህም ከዘላለም ጀምሮ ከእኔ ጋር ሲኖር የነበረውንና የሚኖረውን፣ በጣም የምወደውን እና የማከብረውን ልጄን፣ በእውነት ለእናንተ ያለኝን የፍቅር ስሜት እንዲነግራችሁና በተግባር እንዲያሳያችሁ ወደ እናንተ ላክሁት። እርሱም እያለቀሰ፣ ደስተኛ የምትሆኑበትን መንገድ እየተናገረ፣ እንዲሁም መልካም የሆነውን ነገር እያደረገላችሁ በእኔ ልብ ውስጥ ስለእናንተ ያለውን መልካም ሃሳብ አሳያችሁ። በመጨረሻም እንደማትፈልጉት ብትነግሩትም፣ እርሱ ግን ከእኔ ተለይታችሁ እንድትሞቱ ሳይሆን ለሁልጊዜ ከእኔ ጋር እንድትኖሩ ስለፈለገ በፈቃደኝነት በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ሞተ። ከመሞቱ በፊት ግን፣ ይቅርታ እንዳደርግላችሁ ለመነኝ። እኔም

ይህንን ለማድረግ ከልብ ፈቃደኛ ነኝ። ይቅር እንድላችሁ አንዳች ነገር መከፈል የለባችሁም። ያለባችሁን ዕዳ ሁሉ ልጄ ከፍሎላችኋል። ይህንን ካመናችሁ ወደ እኔ፣ ወደምወዳችሁ አባታችሁ ከመጣችሁ በደስታ ልቀበላችሁ ፈቃደኛ ነኝ። አስታውሱ፣ ወደ እኔ ኑ! የምላችሁ "መልካም አድርጉና እወዳችኋለሁ" ለማለት ሳይሆን፣ እንዲሁ ከነማንነታችሁ ስለምወዳችሁ ነው። ከሞት ያስነሳሁት ልጄም ይወዳችኋል። ለዚህ የፍቅር ጥሪዬ የምትሰጡትን መልስ ለመስማት በጉጉት እጠባበቃለሁ"።

"ይህን ሁሉ መከራ እንዲቀበል የእኔ ፈቃድ ነበር፣ የእርሱም ሞት የኃጢአትን ይቅርታ የሚያስገኝ መስዋዕት ነበር ... ሕይወትን ከሚያሰቃይ ከብዙ መከራ በኋላ፣ የሕይወትን ብርሃን በማየት እንደገና ደስ ይለዋል፣ ያን ሁሉ መከራ የተቀበለውም በከንቱ አለመሆኑንም ይገነዘባል፣ በእርሱ ደስ የሚለኝ የእኔ ፍጹም አገልጋይ ብዙዎች ሊቀበሉት የሚገባውን ቅጣት ተሸክሞ እነርሱን ከኃጢአት ነጻ ያደርጋል" (ኢሳይያስ 53፡10-11)።

በነጻ መስጠትም ሆነ መቀበል ላልለመድን ለእኛ ጥቅም ፈላጊ ሰዎች ይህ መልእክት ሞኝነት ይመስላል። ከራሳቸው ባሻገር በመመልከት በዚህ ባለመልካም ዜና አምላክ እጅ ላይ ሕይወታቸውን የሚያኖሩ ሰዎች ግን ለዘላለም እንዲያው እንደነበሩ አይቀሩም፣ ይለወጣሉ! አዲስ ሕይወትን መኖርን ይጀምራሉ! በነጻ ተወድደዋልና በነጻ ይወዳሉ! በነጻ ተቀብለዋልና በነጻ ይሰጣሉ!

እንደዚህ ያለ፣ ትርጉምና እርካታን የሚሰጥ ሕይወት ሌላ የትም አይገኝም! ይህ ሕይወትን የሚቀይር ኃይል የሚገኘው መልካም በማድረግ፣ ሃይማኖተኛ በመሆን፣ ምጽዋት በመጻወት ወዘተ ሳይሆን፤ ይህንን እስከሞት ድረስ የወደደንን አምላክ የሕይወታችን መሪ በማድረግ ነው። በራስ ወዳድነትና በጥቅም ፈላጊነት ያልተበከሉ መልካም ድርጊቶች የዚህ የፍቅር ግንኙነት ፍሬዎች ናቸው። ለብዙዎች ሞኝነት የሚመስለው ይህ መልዕክት፡- የይቅርታ፣ የደኅንነት እና የበጎ ነገሮች ሁሉ ምንጭ የሆነው የእግዚአብሔር ጥበብ ነው (ኤፌሶን 1፡7-8)። ለእርስዎስ? ገዛው

(ምንጭ፡- የትንቢት ቃል መጽሔት፣ መጋቢት 1993)

ጥያቄና መልስ

2. ሰው ሲሞት ምን ይሆናል?

"ዐፈር ወደ መጣበት መሬት ሳይመለስ፣ መንፈስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ፣ ፈጣሪህን አስብ" (መክብብ 12፡7)። እዚህ ላይ የምንረዳው ሰው ሲሞት አካሉ ወደ አፈር (መሬት)፣ እስትንፋሱ ደግሞ ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር እንደሚመለስ ነው፤ ይህ ክስተት የሚጸመው በዚህ ምድር ላይ በሚገኙ ኃጥአንም ሆነ ጻድቃን ላይ ልዩነት ሳያደርግ ነው። እዚህ ላይ በተጨማሪ ልብ ማለት ያለብን ከላይ የተጠቀሰውን "ሳይመለስ" የሚለውን ቃል ነው። ከቃሉ በምናገኘው መረዳት መሠረት ሞት ማለት ሁሉ ነገር ቀድሞ ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ ማለት ነው፤ ሞት ዐፈሩን (የሰውን አካል) ወደ መሬት፤ እስትንፋሱን ደግሞ ወደ ሰጠው እግዚአብሔር ይመልሳልና። ለምሳሌ በኬምስትሪ ትምህርት መሠረት ውሃ የሁለት እጅ ሃይድሮጅንና የአንድ እጅ ኦክስጅን ውህደት ውጤት ነው። እነዚህ ሁለት ንጥረነገሮች ሲዋሃዱ ውሃ ይፈጠራል፤ ሲለያዩ ደግሞ ውሃ አይኖርም። የሰውም በሕይወት መኖር የአምላክ እስትንፋስና የምድር ዐፈር ውህደት የፈጠረው ሲሆን ሰው ሞተ ስንል ደግሞ የእነዚህ ሁለት ነገሮች ተነጣጥለው ወደ መጡበት መመለስ ነው።



3. ሰው ሲሞት ከእርሱ ወጥቶ ወደ እግዚአብሔር የሚሄደው እስትንፋስ ምንድነው?

"ከመንፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ ከሥራም የተለየ እምነት የሞተ ነው" (ያዕ. 2፡27)። "በውስጤ የሕይወት እስትንፋስ፣ በአፍንጫዬም ወስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ እስካለ ድረስ" (ኢዮብ 27፡3)። በመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ከሰው ወደ እግዚአብሔር የሚመለሰው መንፈስ የሕይወት እስትንፋስ ነው። ይህ እስትንፋስ ወይም መንፈስ ከአካል ተለይቶ የሚቹን ግለሰብ የሚወክል ጥበብ ወይም እውቀት ሆነ ስሜት ወይም ማንነት እንዳለው የሚያስረዳ አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የለም። (ቀጣይ ጥያቄዎች ከመልሶቻቸው ጋር ገጽ 26 ላይ ይገኛሉ)

ቀሬንዮና ኮሮና

ድርባ ፈቃዱ

በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ወቅት፤ ፈረንሳይን ከጀርመኖች እጅ ለማስለቀቅ በተደረገው ፍልሚያ ትልቅ ሚና የነበረው የኖርማንዲው ወረራ ነው። በጦርነቱ ላይ የተሰማሩትን የአሜሪካ ወታደሮች፤ ከአውሮፕላን ዘለው መሬት ላይ ከማረፋቸው በፊት ተኩሰው ሊገድሏቸው የተዘጋጁ ጀርመናዊ የምድር ተዋጊዎች ነበሩ።

በዚያ ውጊያ ከተሳተፉት የአሜሪካ ወታደሮች ውስጥ አንዱ፤ ከመዝለሉ በፊት በአውሮፕላን ውስጥ ያጋጠመውን አንድ ልዩ ክስተት ተርኳል። አብሮት ሲበር የነበረው ወታደር እጆች በደም የረጠቡ መሆናቸውን ተመልክቶ፤ “ምን ሆነህ ነው እጆችህ የሚደሙት?” ብሎ ይጠይቀዋል። ያ ወታደር የራሱን እጆች ትኩሩ ብሎ አይቶ ወደ ጠያቂው እጆች በመመልከት፤ “ያንተም እጆች እኮ በደም ተሸፍነዋል” ብሎ መለሰለት። ሰዎች አሰቃቂ ጣዕር ውስጥ ሲገቡ የደም ሥሮቻቸው ተቀደው ደማቸው ከላብ ጋር በመቀላቀል ከሰውነታቸው ሊፈልቅ እንደሚችል አዋቂዎች ይናገራሉ። ወታደሮቹ ሞትን ፊትለፊት ሊጋፈጡ እንደሚችሉ በማወቅ ላባቸው ደም ሆነ። የሞት ፍርሃት አደማቸው።



ከብዙ የሰው ልጅ ፍርሃቶች ጀርባ የሚያንጉበበው የሞት ፍርሃት ነው። ሞት በበሽታ ወይም በአደጋ መልክ ሲያጠላ “መጨረሻው ምን ይሆን?” ያስብላል። በአሁኑ ጊዜ ዓለምን እያሸበረ ያለው የኮሮና ወረርሸኝ የዚህ ማሳያ ነው። በበሽታው ፍርሃት ምክንያት የዓለም ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሕይወት እየተናጉ ናቸው። ሰዎች መረጋጋት ተስኗቸው አእምሮ በሚያቃውስ ጭንቀት ውስጥ ሲገቡ እናያለን። ታላቁ ፍርሃታቸው የሞት መንጋጋ ውስጥ እንገባ ይሆን የሚለው ነው። ጨለማው መቃብር የታሪካቸው መጨረሻ ስለሚመስላቸው፤ ዋና ጭንቀታቸው ከሰው ቁጥጥር ድንገት አፈትልኮ የሚያመልጠውን ምድራዊው ሕይወት ማራዘም ሆኗል። ኮሮናን ለመከላከል ብዙ ጥረትና ገንዘብ የሚከፈልበት ምክንያቱ ይህ ነው።

ለመሆኑ ኮሮና የሚፈራው ለምንድነው? ሞትን የምንፈራው ለምንድነው? ከዓቅማችን በላይ ሆኖ በእኛ ላይ ኃይል ያለው ነገር መሆኑ በእርግጥ አስፈሪ ነው። ከዚህ ሌላ ግን የሞት አለቃ ሆኖ ሰዎችን በሽብር ለማንበርከክ የሚፈልግ ረቂቅ ኃይል እንዳለ ደግሞ ቃሉ ያስተምራል።

ሰይጣንና ሞት መሠረታዊ ትሥሥር አላቸው። ሞት የሕይወት ተቃራኒ ስለሆነ ሕይወት ከሆነው አምላክ የተለየ ሁሉ ለሞት ተጋላጭ ነው። ይህ ተጋላጭነት እንዲስፋፋ ኃጢአትና እርኩሰትን ተወዳጅ አድርጎ ሰዎችን ለዘመናት ከፈጣሪ ሲለይ የቆየው ሰይጣን ነው። በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን አምላክ ባህርይ ሳናስተውል ሰይጣን በዘላለማዊ ድንጋጤና መንቀጥቀጥ ውስጥ ታስረን እንድንኖር ይፈልጋል። ታሪክና ዕለታዊ የዜና ዘገባዎች የሚያሳዩት ይህ እኩይ ዓላማው እንደተሳካለት ነው።

ኃጢአት ባለበት ሞት አለ። ሞት ባለበት ሁሉ ደግሞ ገዢ ፍርሃት አለ። ሲያል በነገሠበት ቦታ መኖር ሞትን በመጠበቅ መንገዳገድ ማለት ነው። የመድኀን ድርጅቶች ለአደጋዎችና ለሰው ፍርሃት ከለላ እንሆናለን ብለው ትርፋማ ንግድ ቢመሠርቱም፤ ከሞትና ከሞት ፍርሃት ግን ማንንም ማላቀቅ አይችሉም። ወደ መቃብር ቁልቁል የሚያንደረድረው መንገድ “የኑሮ ትግል” ሳይቀናቸው በተሰዉ ሰዎች የተነጠፈ ነው። ታዲያ መፍትሄው ምንድነው? የሞት እውነታ የእኔነትን ክብር ስለሚነዳ ከውርደት ለመሸሽ ሰዎች ከመፍትሔው ይልቅ ከህደትን ይመርጣሉ። “‘ከሞት ጋር ቃል ኪዳን ገብተናል፤ ከሲኦልም ጋር ስምምነት አድርገናል፤ ውሸትን መጠጊያችን፣ ሐሰትን መደበቂያችን አድርገናል፤ ታላቅ መቅሠፍት እየጠራረገ ሲያልፍ፣ ሊነካን አይችልም’ በማለት ታብየቻችኋል” (ኢሳ. 28፡15)። ምድራዊ መፍትሔዎች ዘላለማዊ አይደሉም። የሕክምና ሳይንስ፣ የፖለቲካ ለውጥ ወይም አንዳንድ ሐሰተኛ መምህራን እንደሚሉት የሰዎችን “ዕምቅ መለኮታዊ ባህርይ” ማዳበር ሞትን አያሸንፉም።

የሞት መድኃኒቱ ሞት ነው። በሞት ፍርሃት ምክንያት የሚንቀጠቀጠው ሥጋ ካልሞተ መዳን አንችልም። ጌታችን እንደተናገረው፤ “የስንዴ ቅንጣት መሬት ላይ ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ

ፍሬ ታፈራለች" (ዮሐ. 12:24)። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ወደነገሠባት ምድራችን የመጣው ሊሞት ነው። በመሞቱ ከሰይጣን ጋር ፊትለፊት ተጋጥሟል። ክርስቶስ ከሞት ለማምለጥ ሳይሞክር፤ የማናውቀውን ፍርሃትና ውርደት ተጋፍጦ በታላቅ ሐዘን አንገቱን አዘቅዝቆ ሞቷል። እርሱ ግን ተራ ሞት አልሞተም። ከመቃብር ማዶ ያለውን የብርሃን ትንሳኤና ሕይወት በጉልህ የሚያሳይ ሞት ነው የቀመሰው።

"ልጆቹ በሥጋና በደም እንደሚካፈሉ እርሱ ራሱ ደግሞ ያንኑ ተካፈለ፤ ይኸውም በሞት ላይ ኀይል ያለውን ዲያቢሎስን በሞቱ ኀይል እንዲደመስስ ነው። እንዲሁም በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በሞት ፍርሀት ባርነት የታሰሩትን ነጻ እንዲያወጣ ነው" (ዕብ. 2:14-15)።

ክርስቶስ በምድር የለበሰው እኛን በሞት ፍርሃት አስሮ የሚያንገላታንን ሥጋ ነው። ፍርሃትና አለማመን ያስቸገረውን ሥጋ ያሸነፈው እንደኛ ሰው ሆኖ ነው። በዚህ ሥጋ ውስጥ ኖሮ ተስፋ በሚያስቆርጡ ሥነልቦናዊ ስቃዮች ያልተፈተነ ሰው የለም። በብቸኝነት ጨለማ ውስጥ ሁሉም የሚያውቀው አስፈሪና ጥንታዊው የሞት ፉጨት አለ። ወደዚህ ጥልቅ የስሜት ጓዳ ገብቶ ነው ጌታችን ከጠላት ጋር ፊትለፊት የተዋጋው።

ስለ ውጊያው ጌታችን ምን ብሏል? "ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዝናለች" (ማቴ. 26:38)። በክርስቶስ ላይ የተከመረው ሐዘን ፊቱን በደም ላብ አጥቦ ወደ ሞት አፋፍ አደረሰው። ያንን ሐዘንና የደም ላብ እንዴት አሸነፈው? "ኢየሱስ በዚህ ምድር በኖረበት ዘመን ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው ጸሎትንና ልመናን ከታላቅ ጩኸትና ከእንባ ጋር አቀረበ፤ ፍጹም ትሑት ሆኖ በመታዘዙም ጸሎቱ ተሰማለት። የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም እንኳ፣ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ በዚህም ፍጹም ሆኖ ከተገኘ በኋላ፣ እርሱን ለሚታዘዙ ሁሉ የዘላለም ድነት ምክንያት ሆነላቸው" (ዕብ. 5:7-9)። የጌታችን ጩኸትና እንባ በፍርሃትና ጣዕረ ሞት ለዘመናት የተሰቃየውን የሰውን ዘር ሁሉ የሚጠቀልል ነው። በርሱ የሕመም ጩኸት ምክንያት እኛ የደስታ መዝሙር ተቀበልን። እንባው እንባችንን አጥቦ በደኅንነት ሳቅ እንድንፈነድቅ አድርጓል። ሊውጠን ያሰፈሰፈው የሲዖል ስግብግብ አፍ ተዘግቶ የሰማይ ደጆች ወለል ብለው ተከፈቱ።



ቀራንዮ ስለ ሞት አሰቃቂነትና ስለ እግዚአብሔር ጥልቅ ፍቅር ይመሰክራል። ሞትን እንዳንፈራ ከመቃብር ባሻገር ያለውን ዘላለማዊ ሕይወት አሳይቶናል። ከሁሉ በላይ ግን ፍቅሩን አቅምሶ ፍርሃት ከልባችን እንዲወገድና በነፃነት እንድንኖር ጠርቶናል። "በፍቅር ፍርሀት የለም፤ ፍጹም ፍቅር ግን ፍርሀትን አውጥቶ ይጥላል፤ ፍርሀት ከቅጣት ጋር የተያያዘ ነውና። የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም" (1ዮሐ. 4:18)።

ሰሞኑን በፍጥነት እየተዛመተ ያለው የኮሮና በሽታ በሰዎች ልብ መደናገጥን ፈጥሯል። ሞትን በመፍራት ሰዎች ሥራቸውንና ማኅበራዊ ሕይወታቸውን ሸሽተው፣ በር ዘግተው እንዲቀመጡ አድርጓል። ይህ ሁኔታ የተሻለ ሰማያዊ ሕይወት እንዳለን ረስተን በምድሩ ኀደሎ ሕይወት ላይ በፍርሃት እንድንጠመድ የሚያስገድድ ይመስላል። ሞትን ያሸነፈው አምላክ ግን በኮሮና ፍርሃት እንድንቀጠቀጥ አይፈልግም። ፍቅሩ በልባችን ካለ ምንም ሊያሸብረን አይገባም። "እጁን በላዬ ጭኖ እንዲህ አለኝ፤ 'አትፍራ፤ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም እኔ ነኝ፤ እኔ ሕያው ነኝ፤ ሞቼ ነበር፤ እነሆ አሁን ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲኦል መክፈቻም በእጄ ነው" (ራዕ 1:17-18)።

በመጨረሻው ዘመን፤ ዓለም ታይቶ በማይታወቅ መከራ ውስጥ ስትገባ ድል ነሺ የሚሆኑት በሞት ፍርሃት ላይ ድል የተቀዳጁ ናቸው። በፈተና ከመብረከረክ ይልቅ የክርስቶስን መስዋዕታዊ ሕይወት በማስታወስ በፍቅሩ ኃይል የሞትን ፍርሃት ፊትለፊት ይጋፈጣሉ።

"እነርሱም በበጉ ደም፣ በምስክርነታቸውም ቃል፣ ድል ነሱት፤ እስከ ሞት ድረስ እንኳ፤ ለነፍሳቸው አልሳሱም" (ራዕ 12:11)። ይህን ድል ለመቀዳጀት ያለን የልምምድ ጊዜ አሁን ነው። በየቀኑ አይኖቻችንን ወደ ቀራንዮ ከፍታ ማዞር ያስፈልገናል። የአምላክን ፍቅር ያስተዋለ ሰው ለምድራዊ ነፍሱ በመሣሣት አላስፈላጊ ጭንቀት ውስጥ አይገባም፤ መሣሣት የፍርሃትና የሞት ነውና። ነፃነትና የተትረፈረፈ ሕይወት ግን ቀራንዮ ላይ በፈሰሰው በግ ደም ተገኝቷል። ይህንን ታሪካዊ ድል ለሚዘክረው ፋሲካ እንኳን አደረሰን! ገዚው

4. ታዲያ ነፍስ ማለት ምን ማለት ነው?

ከላይ በተጠቀሰው ዘፍጥረት 2፡7 መሠረት "ነፍስ" ማለት የሕይወት እስትንፋስ ከአፈር ከተሠራው አካል ጋር ሲገናኝ የሚፈጠረው ሕይወት ያለው ፍጡር ነው። ይህ ነፍስ ወደ ጎልውና የመጣው እስትንፋስና አካል ተገናኝቶ ወይም ተደምሮ በመሆኑ ሁለቱ በተለያዩ ቀን የነፍስ ጎልውና ያከትማል። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰው በሕይወት እስካለ ድረስ "ነፍስ" ተብሎ እንደሚጠራ እናነባለን። በቀላሉ "አምስት ሰዎች" ያሉበት ቦታ "አምስት ነፍሳት" ያሉበት ሊባል ይቻላል።

5. ነፍስ ይሞታል?

"ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች" (ሕዝ. 18፡20)። "በባሕርም ከሚኖሩት ሕይወት ያለበት ነፍስ ሁሉ ሞተ" (ራዕይ 16፡3)። እንደ እግዚአብሔር ቃል አገላለጽ ነፍስ ይሞታል። ምክንያቱም የአምላክ እስትንፋስና የአፈር ውጉድ የሆነው ሰው ነፍስ ነው፤ ነፍስ (ሰው) ደግሞ ይሞታል፤ ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ሟች ናቸው (ኢዮብ 4፡17)። የማይሞተው እግዚአብሔር ብቻ ነው (1ጢሞ. 6፡15፣16)። ይህ በመሆኑም ሰው ሲሞት ተለይታ የምትወጣ የዘላለማዊ ነፍስ (የማይሞት ነፍስ) አለች የሚለው ጽንሰሀሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

6. መልካም ሰዎች ሲሞቱ ወደ ሰማይ ይሄዳሉ?

"በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉ ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ" (ዮሐ. 5፡28፣29)። "ወንድሞች ሆይ፥ ስለ አባቶች አለቃ ስለ ዳዊት እንደ ሞተም እንደ ተቀበረም ለእናንተ በግልጥ እናገር ዘንድ ፍቀዱልኝ፤ መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ ነው። ... ዳዊት ወደ ሰማያት አልወጣምና" (የሐዋ. 2፡29፣34)። ሰዎች ሲሞቱ ወደ ሰማይም ሆነ ወደ ገሃነም አይሄዱም። ይልቁኑ እስከ ትንሳዔ ቀን ድረስ በመቃብራቸው ሆነው እንደ ዳዊት የትንሣኤን ቀን ይጠብቃሉ።



7. ሰው ከሞተ በኋላ ምን ያህል ያስተውላል?

"ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉና፤ ሙታን ግን አንዳች አያውቁም፤ መታሰቢያቸውም ተረስቷልና ከዚያ በኋላ ዋጋ የላቸውም። ፍቅራቸውና ጥላቸው ቅንዓታቸውም በአንድነት ጠፍቶአል፥ ከፀሐይ በታችም በሚሠራው ነገር ለዘላለም እድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም። ... አንተ በምትሄድበት በሲኦል ሥራና አሳብ እውቀትና ጥበብ አይገኙምና እጅህ ለማድረግ የምታገኘውን ሁሉ እንደ ኃይልህ አድርግ" (መክብብ 9፡5፣6፣10)። "አቤቱ፥ ሙታን የሚያመሰግኑህ አይደሉም፥ ወደ ሲኦልም የሚወርዱ ሁሉ" (መዝ. 115፡17)። በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት ሙታን አንዳች አያውቁም።

8. ሙታን ሕያዋን የሚሠሩትን ያውቃሉ? ከሕያዋን ጋር መገናኘት፣ መነጋገር ይችላሉን?

"ሰውም ተኝቶ አይነሣም፤ ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ አይነቃም፥ ከእንቅልፉም አይነሣም። ... ልጆቹ ቢከብሩ አያውቅም፤ ቢዋረዱም አያይም" (ኢዮብ 14፡12፣21)። "ከፀሐይ በታችም በሚሠራው ነገር ለዘላለም እድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም" (መክብብ 9፡6)። ሙታን በዚህ ምድር ላይ በሚፈጸመው ማንኛውም ነገር ላይ ተሳትፎ የላቸውም። ስለዚህ ማንኛውንም ሕያው ሰው አያናግሩም፤ በዚህ ምድር ላይ የሚፈጸምን አንዳች ነገር አያውቁም፤ ሃሳባቸው ሁሉ ጠፍቷል (መዝ. 146፡4)።

9. ክርስቶስ ሞትን ዕንቅልፍ ይለዋል (ዮሐ.11፡11-14)፤ታዲያ ሙታን ለምን ያህል ጊዜ ያንቀላፋሉ?

"ሰውም ተኝቶ አይነሣም፤ ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ አይነቃም፥ ከእንቅልፉም አይነሣም" (ኢዮብ 14፡12)። "የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ" (2 ጴጥ. 3፡10)። ሙታን በመቃብራቸው ውስጥ በእንቅልፍ የሚቆዩት ክርስቶስ ዳግም እስከሚመጣ ነው። እስከዚያ ድረስ ግን አንዳች የሚያውቁት ሳይኖር በመቃብራቸው ውስጥ ይቆያሉ፤ ያንቀላፋሉ። ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ የሞቱት ጻድቃን ይነሳሉ (1ተሰ. 4፡16፣17፤ 1ቆሮ. 15፡51-53)። ሙታን በትንሳኤ ቀን በማይሞት ሥጋ ይነሳሉ። ጌታን በአየር ላይ ለመገናኘት ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ። እንግዲህ ሰዎች እንደሞቱ ወደ ሰማይ የሚሄዱ ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ የትንሳኤን አስፈላጊነት ይህን ያህል አጉልቶ አይናገርም ነበር። ገዚው (ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ)

ይህ ማን ነው?

“ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ መላው ከተማ፦ **ይህ ማን ነው?** ብሎ ተናወጠ”፤ ሉቃስ 19፡37 እና ማቴዎስ 21፡10፤

አዳም ቢጠየቅ፤ የእባቡን ጭንቅላት የሚቀጠቅጠው የሴቲቱ ዘር ነው ብሎ ይመልሳል፤ ዘፍጥረት 3፡15

አብርሃም ደግሞ “የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅ የልዑል እግዚአብሔር ካህን” ይላል፤ ዘፍጥረት 14፡18

ያዕቆብ፤ ገሸርነት የተገባው ነገደ ይሁዳ ነው ይለዋል፤ ዘፍጥረት 49፡10

ኢሳይያስ፤ “አማኑኤል”፤ “ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ” በማለት ይመልሳል፤ ኢሳይያስ 7፡14፤ 9፡6

ኤርምያስ፤ የዳዊት ቤት ጻድቅ ቅርንጫፍ፤ “እግዚአብሔር ጽድቃችን” ነው ይላል፤ ኤርምያስ 23፡6

ዳንኤል፤ መሢሕ ነው በማለት ይመልሳል፤ ዳንኤል 9፡25

ሆሴዕ፤ “ሁሉን የሚገዛ አምላክ እግዚአብሔር፥ የሚታወቅበት ስሙም እግዚአብሔር ነው”ይላል፤ ሆሴዕ 12፡5

መጥምቁ ዮሐንስ፤ “የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ” በማለት ስሙን ያውጃል፤ ዮሐንስ 1፡29

ኃያሉ አምላክ እግዚአብሔር፤ “እርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ” በማለት ከዙፋኑ ያውጅለታል፤ ማቴዎስ 3፡17

እኛ ተከታዮቹ ደግሞ፤ ይህ መሲሑ ኢየሱስ ነው፤ የሕይወት ጌታ፤ የዓለም መድኅን በማለት እንመሰክራለን፤

የጨለማው ኃይላት፤ “የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ... ማን እንደ ሆንህ አውቀናል፥ የእግዚአብሔር ቅዱስ” ነህ በማለት ዕውቅና ይሰጡታል (ማርቆስ 1፡24)።

(የዘመናት ምኞት፤ ገጽ 579)



ወእመሰ ኢይትነሥኡ ምዉታን

ክርስቶስኬ ኢተንሥአ እምዉታን።

ወእመሰ ክርስቶስ

ኢተንሥአ እምዉታን

ከንቱ ሃይማኖትክሙ

ወዓዲክሙ ሀሎክሙ

ውስተ ኃጢአትክሙ።

ሙታን የማይነሡ ከሆነ

ክርስቶስ አልተነሣማ፤

ክርስቶስም ካልተነሣ

እምነታችሁ ከንቱ ናት፤

እስከ አሁን ድረስ

በኃጢአታችሁ አላችሁ።

፩ቆሮንቶስ ፲፭፡ ፲፮-፲፯